# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የኢትዮጵያ የደን ልማት

# የ2015 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር የስራ አፈጻጸም

# ሪፖርት

ሚያዝያ 2015

አዲስ አበባ

## ማውጫ

1. ድርሞ/Executive Summary/ .... 2
2. መግቢያ .... 4
3. የተቋሙ ርዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች .... 5
3.1. ርዕይ .... 5
3.2. ተልዕኮ .... 5
3.3. እሴቶች .... 5
4. በቁልፍ የውጤት አመልካቾች ላይ የተመሰረተ የዘጠኝ ወራት የፊዚካል ስራ አፈፃፀም ትንተና .... 6
5. የተቋሙ የፋይናንስ/ በጀት አፈፃፀም .... 28
6. የተቋሙ የኦዲት ግኝት ምልከታ .... 29
7. ተቋማዊ ለውጥና የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም .... 30
8. የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች አፈጻጸም .... 31
9. የዋና ዋና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም .... 32
10. የዕቅድ አፈጻጸም ክትትል እና ግምገማ ሥራዎች .... 32
11. በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተወሰዱ/ሊወሰድ የሚገባቸው የመፍትሔ እርምጃዎች .... 32
12. ማጠቃለያ .... 33
13. አባሪ .... 34

## 1. ድርሞ/Executive Summary/

የደን ሀብት በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ጥቅሞችና ግልጋሎቶች አሉት፡፡ ይህንን ግልጋሎት ለማሳደግ በ2015 በጀት ዓመት በርካታ ተግባራትን ለማከናወን በዕቅድ ተይዞ ወደስራ ተገብቷል፡፡

በዘጠኝ ወር ውስጥ የሚጠበቁ ውጤቶችን ለማሳካት እንዲያስችል የ2014 በጀት ዓመት አፈፃፀምን ተገምግሞ የተወሰደውን ግብዓት መሰረት በማድረግ የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ተዘጋጅቶ በማኔጅመንት፣ በሰራተኞች እንዲሁም በባለድርሻ አካላት ከተገመገመ በኂላ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በተጨማሪም ለስራው አስፈላጊ ግብዓቶችን የማሟላት፣ የአሰራር ስርዓቶችን የመዘርጋትና የማጠናከር እንዲሁም አዲሱን የተቋም አደረጃጀት ተከትሎ በመሰራት ላይ ያለውን የመስሪያ ቤቱን መዋቅር ተጠናቆ የሰራተኛ ድልድል በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በዘጠኝ ወራት ውስጥ ከተከናወኑ ዋና ዋና ስራዎች መካከል ከሮያሊቲ እና ከተለያዩ የደን ምርት ውጤቶች ሽያጭ በዘጠኝ ወር ውስጥ 180 ሚልየን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በተሰራው ስራ 246.699 ሚልየን ብር የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100 % በላይ ሆኗል፡፡ አፈፃፀሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት የተሻለ ክትትልና ድጋፍ በመደረጉ እና ክልሎችም ትኩረት ስለሰጡት ነው፡፡

በዘጠኝ ወራት ውስጥ ለ220,000 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በደን ጥበቃ፤ የደን ምርቶችን በመጫን፤ በማጓጓዝና በማውረድ፣ በችግኝ ተከላና እንክብካቤ፣ በእንጨት ኢንዱስትሪ፤ ኢንተርፕራይዞች፣ የደን ምርት ውጤቶችን በማቅረብ፤ በመቸርቸርና በመላክ፣ በከሰል ማክሰል እና በመሳሰሉት የስራ መስኮች በአጠቃላይ ለ259,920 ዜጎች በቋሚ የስራ ዕድል 32,660 (ወንድ 20,714 ሴት 11,946) እና በጊዚያዊ 227,260 (ወንድ 151,958 ሴት 75,302) የስራ ዕድል ለመፍጠር የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ አፈፃፀሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በመንግስት፣ በህበረተሰቡ እና በሌሎች ባለድርሻ አካላት ትኩረት በማግኘቱ እንዲሁም በግለሰቦች፤ በኢንተርፕራይዞች እና ኢንዱስተሪዎች በኩል የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ስራ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ በመምጣቱና የስራ ዕድል በመፈጠሩ ነው፡፡

በ600,000 ሄ/ር መሬት ላይ ተከላ ለማካሄድ ታቅዶ በ748,000 ሄ/ር ተከላ ማካሄድ ተችሏል፡፡ ከዚህም ውስጥ የቀርቀሃ ደን ልማት በ20,000 ሄ/ር መሬት ተከላ ለማካሄድ ታቅዶ 77,413.44 ሄ/ር መሬት ላይ ለመትከል ተችሏል፤ አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ ለተከላ በተዘጋጁ ቦታዎች 3 ቢሊዮን ደረጃቸውን የጠበቁ ችግኞች ተፈልተው እንዲተከሉ ለማድረግ ታቅዶ 3.415 ቢሊዮን ከ100% በላይ የደን ችግኞች መትከል ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ 48.383 ሚሊዮን የቀርከሀ ችግኝ ነው፡፡ አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ለደን ልማት የተሰጠው ትኩረት ከፍተኛ በመሆኑና ከመደበኛ በተጨማሪ የፕሮጀክቶችና የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡

የችግኞችን ጽድቀት መጠን ለማሳደግ የተለያዩ የድህረ ተከላ የእንክብካቤ ስራዎች (የአረምና ኩትኳቶ እና አልፎ አልፎ ፍግ መጨመርና ውሃ የማጠጣት) በማካሄድ የዓመቱ የመጀመሪያ ዙር የጽድቀት መጠን 85 በመቶ ለማሳደግ ታቅዶ በአማካኝ 88.2 በመቶ የችግኝ የጽድቀት መጠን ተመዝግቧል፡፡

በዘጠኝ ወራት ውስጥ 19.2 ሚ/ሄር ነባር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ታቅዶ 18.68 ሚሊዮን ሄ/ር ለመጠበቅ ተችሏል። ከዚህም ውስጥ 2.16 ሚሄ/ር ነባር የተፈጥሮ ደኖች ላይ አሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓትን በመተግበር በዘላቂነት እንዲጠበቁና ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ተችሏል።

በዘጠኝ ወራት ውስጥ ለ75,000 ሄክታር ደኖች የማኔጅመንት ፕላን እንዲዘጋጅና እንዲተገበር ለማድረግ ታቅዶ 169,074.45 ሄ/ር ደኖች የማኔጅመንት ፕላን የተዘጋጀላቸው ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው። አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ከመደበኛ ውጪ በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም መስክ ልዩ ድጋፍ በሚያደርጉ መንግሳታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በGIZ በአማራ ክልል ደን ኢንተርፕራይዝና የተለያዩ ፕሮጀክቶች በተገኘ ድጋፍ የተከናወነ በመሆኑ ነው።

በምርምር ስራዎች በዘጠኝ ወሩ 13 የምርምር ውጤቶችን ለማውጣት ታቅዶ በድምሩ 12 ውጤቶች ማውጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃሙም 92.3% ሆኗል።

በዘጠኝ ወራት ውስጥ በመደበኛ በጀት ከተለቀቀው 156,883,455.35 ብር ውስጥ 149,260,186.11ብር ጥቅም ላይ ለማዋል የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 95.1% ነው። በካፒታል በጀት ከተለቀቀው 55,220,000.00 ብር ውስጥ 33,667,491.38 ብር ጥቅም ላይ ለማዋል የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 61% ነው። የካፒታል በጀት አፈፃፀሙም ያነሰበት ምክንያት የሁለት ላቦራቶሪዎች ግንባታ በመዘግየቱ ነው። የችግሩ መንስኤ በሃገር አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የግንባታ ማቴሪያል እጥረት እና ዋጋ ንረት በመከሰቱ ነው። ይህንም ችግር ለመፍታት ተቋሙ ከተቋራጮች እና አማካሪው ድርጅት እንዲሁም ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ጋር ውይይት በማድረግ የዋጋ ማስተካካያ ቀርቦ ተቀባይነት አግኝቷል።

በአጠቃላይ የዘጠኝ ወራት የተቋሙ የመደበኛና የካፒታል በጀት አጠቃቀም 86.2% ሲሆን የፊዚካል ስራዎች አፈጻጸም ደግሞ 95.8% ነው።

## 2. መግቢያ

የደን ሀብት በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ጥቅሞችንና ግልጋሎቶችን ያበረክታል፡፡ ደን ለማገዶ እና ለግንባታ፣ የቤተሰብ ገቢን እና የሀራችንን ኢኮኖሚ ለማሳደግ፣ የአፈር ክለት ለመቀነስና ለምነትን ለመጨመር፣ በውሀ አካላት ላይ የሚፈጠረውን ደለል ለመቀነስ፣ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለመቋቋም፣ ለዱር እንስሳት መጠለያነት እና የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሚያበረክታቸው አስተዋጽኦዎች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ስለሆነም የኢትዮጵያ ደን ልማት በበጀት ዓመቱ በደን ልማት፣ ጥበቃ፣ አያያዝ እና አጠቃቀም እንዲሁም በደን ምርምር ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን ቀርፆ እንዲሁም የልማት ስራዎችን አቅዶ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተጀመረው ሀገራዊ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ከክልሎች፣ ከተማ መስተዳድሮችና ከሚመለከታችው አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት መጠነ ሰፊ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚሁ ፕሮግራም በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሀይማኖት ተቋማት ጭምር እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

ይህ ሪፖርት በባለፉት ዘጠኝ ወራት በተቋማችን የተከናወኑትን ዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም አካቶ የያዘ ሲሆን ሪፖርቱ በሃገር አቀፍ ደረጃ በደን ልማት፣ ጥበቃ፣ እንክብካቤ፣ አጠቃቀም እና ምርምር ላይ የተከናወኑ ስራዎችን አፈፃፀም የሚያሳይ ሲሆን የተከናወኑ ዝርዝር ስራዎች አፈፃፀም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 3. የተቋሙ ርዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች

### 3.1. ርዕይ

በ2022ዓ.ም ዘላቂ ደን ልማት፣ አያያዝና አጠቃቀምን በማረጋገጥ በአፍሪካ የላቀ የደን ልማት ተቋም ሆኖ መገኘት፡፡

### 3.2. ተልዕኮ

የደን ሀብታችን በዘላቂነት እንዲጠበቅ፣ እንዲለማ፣ የተራቆቱ አካባቢዎች እንዲያገግሙ እና የደን ውጤቶችን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ አገራችን ከደን ሀብት የተሻለ ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊ እና ስርዓተ-ምህደራዊ ጠቀሜታን እንድታገኝ በማድረግ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖን በመቋቋም ለሁለንተናዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ማድረግ፡፡

### 3.3. እሴቶች

- ግልጸኝነት
- ቁርጠኝነት
- አጋርነት
- ጥራት
- ቅልጥፍና
- ውጤታማነት
- የሙያ ስነ-ምግባር
- ፈጠራ

## 4. በቁልፍ የውጤት አመልካቾች ላይ የተመሰረተ የዘጠኝ ወራት የፊዚካል ስራ አፈፃፀም ትንተና

### ግብ 1.የተገልጋዮች እርካታን ማሳደግ

- ከተገልጋዮች በስልክና በአካል ለቀረቡ የሙያ ድጋፍ ጥያቄዎች ተገቢው የማማከር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡
- ከሀዋሳ፣ ጅማ እና ወሎ ዩኒቨርሲቲ ለመጡ 5 ተማሪዎች ለመመረቂያ ፅሁፍ ማሟያ እና ለኢንተርንሺፕ የተግባር ስልጠና ተሰጥቷል እንዲሁም የሚፈልጉትን መረጃ እንዲያገኙ ተደርጓል፣
- የተቋሙን አገልግሎት ፈልገው የመጡ ተገልጋዮች በአግባቡ እንዲስተናገዱ ተደርገዋል፡፡
- ከደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልላዊ መንግስት የደን አካባቢ ጥበቃና ልማት ቢሮ የመጡ የሥራ ሐላፊዎችና ባለሙያዎች በተቋማችን የላብራቶሪ አሰራር፣ አደረጃጀትና የላብራቶሪ መሳሪያዎች አጠቃቀም ዙሪያ የአንድ ቀን ገለጻ እና ልምድ የማካፈል ሥራ ተሰርቷል፡፡
- በዛፍ ዘር አገልግሎት ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ እና የተገልጋይ እርካታ ደረጃን ለማወቅ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ደረጃውን የጠበቀ ቅጽ ተዘጋጅቶ የተገልጋይ እርካታ መረጃ እየተሰበሰበ ይገኛል፡፡
- ለአንድ የደን ልማትና ተያያዥ ስራዎች ድርጅት የዘር ብቅለት ሙከራ የትብብር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡
- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ/ቤተክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን በሰሜን ሸዋ ሀ/ስብከት ልማት መ/ግብር ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በኩል በሰ/ሸዋ ዞን ገዳማት ዉስጥ ሊገነቡ ለታሰቡት የማህበራዊ ዘር ባንኮች የመስክ ጉብኝት፣ የዳሰሳ ጥናት እና የማማከር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

### የተገኘ ውጤት

- ተገልጋዮች የፈለጉትን አገልግሎትና መረጃ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

### ግብ 2. የሀብት አጠቃቀምና ዉጤታማነትን ማሳደግ

- የተቋሙን ስራዎች በቅንጅትና ዕቅድን መሰረት አድርጎ በመስራት አላስፈላጊ ወጪዎችን ለመቀነስ ጥረት ተደርጓል፣
- በ2013 እና በ2014 በጀት ዓመት በፌዴራል ዋና ኦዲተር እና በውስጥ ኦዲተር በተከናወነው የፋይናንስ እና የንብረት የኦዲት ግኝቶች መሰረት በማድረግ የማስተካከያ መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ አፈፃፀሙ ላይ እርምጃ ተወስዶ ቀሪዎች ላይ ክትትል በመደረግ ላይ ነው፣
- በተከናወኑ ኦዲቶች ሁሉ የበላይ አመራርን ያካተተ የኦዲት መውጫ ስብሰባ በማድረግ ባለፉ ስራዎች የተፈጠሩ ክፍተቶች እንዲታረሙና በቀጣይ ስራ ግልፅነት እንዲፈጠር የማድረግ ስራ ተሰርቷል፣
- በዋናው መስሪያ ቤትና በማዕከላት በውስጥ ኦዲት የኢንስፔክሽንና ክትትል ስራዎች እና የንብረትና ሂሳብ ምዝገባ ወቅታዊነት የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም የፋይናንስ እና የግዥ መመሪያን መሰረት በማድረግ

የተመደበ ንብረትና በጀትን በአግባቡ መጠቀምና ለታለመለት ዓላማ ብቻ እንዲውል የድጋፍና ክትትል ስራዎች ተከናውነዋል፣

- በጀት አጠቃቀምን ውጤታማ እና ወጭ ቆጣቢ እንዲሆን ለማስቻል ለተቋሙ ከመንግስት የተመደበውን በጀት አሳታፊ በሆነ መንገድ በፕሮግራም በጀት መርህ መሰረት ፕሮግራሞችን፣ ፕሮጀክቶችን፣ ዋና ዋና ተግባራት እና የሚያስገኙትን ውጤት ታሳቢ ያደረገ የበጀት ድልድል ስራ ተከናውኗል፣
- በውጭ እና በውስጥ ኦዲተሮች እንዲስተካከሉ ሪፖርት የቀረበባቸውን ጉዳዮች ተግባራዊነት ለመከታተልና ለማስፈጸም በታቀደው መሰረት ክትትል ተደርጓል፣
- በዘጠኝ ወሩ ውስጥ ለተቋሙ ከተለቀቀው መደበኛ በጀት 156,883,455.35 ብር ውስጥ 149,260,186.11 ብር ጥቅም ላይ ለማዋል የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 95.1% ሲሆን በካፒታል በጀት ከተለቀቀው 55,220,000.00 ብር ውስጥ 33,667,491.38 ብር ጥቅም ላይ ለማዋል የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 61% ነው። የካፒታል በጀት አፈፃፀሙም ያነሰበት ምክንያት የሁለት ላቦራቶሪዎች ግንባታ በመዘግየቱ ሲሆን የችግሩ መንስኤ በሃገር አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የግንባታ ማቴሪያል እጥረት እና ዋጋ ንረት በመከሰቱ ነው። ይህንም ችግር ለመፍታት ተቋሙ ከተቋራጭ እና አማካሪው ድርጅት እንዲሁም ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ጋር ውይይት በማድረግ የዋጋ ማስተካካያ ቀርቦ ተቀባይነት አግኝቷል። ስለዚህም አጠቃላይ የተቋሙ የመደበኛና ካፒታል በጀት አፈፃፀም 86.2% ሆኗል።

## በልማት አጋር አካላት ድጋፍ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች የበጀት አፈፃፀም

- CFSDP ብር 33,162,803 ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ ብር 32,499,546.94 (98%) ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል።
- በሬድ ኢንቨስትመንት ፕሮግራም (RIP-AR/ANR) ብር 227,598,293.69 ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ ብር 200,528,364.95 (88.11%) ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል።
- የከፍታማ ቦታዎች የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ፕሮጀክት ብር 27,629,185.88 ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ ብር 27,629,185.88 (100%) ስራ ላይ ማዋል ተችሏል።
- በደን ምንጣሮና መመናመን የሚለቀቅ ሙቀት አማቂ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ሴክሬታሪያት ደረጃ ብር ብር 199,257,258.09 ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ ብር 147,450,370.98 (74%) ስራ ላይ ማዋል ተችሏል። አፈፃፀሙ ያነሰበት ምክንያት ገንዘቡ ከድጋፍ ሰጭው በወቅቱ ስላልተለቀቀ እና የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው አካላት በወቅቱ ሂሳብ ለማወራረድ ባለመቻሉ ነው።
- የደን ሴክተር ትራንስፎርሜሽን ዩኒት (FSTU) ብር 88,640,258 ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ ብር 58,622,819.9 (66.14%) መጠቀም ተችሏል። አፈፃፀሙ ያነሰበት ምክንያት ገንዘቡ ከኤንባሲ በወቅቱ ስላልተለቀቀ እና የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው አካላት በወቅቱ ሂሳብ ለማወራረድ ባለመቻላቸው ነው።
- በCRFL ፕሮጀክት 34,025,405.80 ብር ጥቅም ላይ ለማዋል ታቅዶ 32,815,735.74 ብር (96.44%) ጥቅም ላይ ውሏል።

### የተገኘ ውጤት

- የተለቀቀውን በጀት በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ መዋሉ፡፡

### ግብ 3- የሀብት ግኝትን ማሳደግ

- ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን የልማት ተራድኦ ድርጅት ጋር በጋራ የሚሠራ የ church forest governance የምርምር ተግባር ለመስራት የሚያስችል ብር 260,000 (ሁለት መቶ ስልሳ ሺ ብር) ተገኝቷል፡፡
- ከዛፍ ዘር ሽያጭ 161,870 ብር ተገኝቷል፡፡
- ከUNCCD አለም አቀፍ ስምምነት 120,000 USD ማግኘት ተችሏል፡፡
- በከተሞች የአረንጓዴ ልማት ስራዎችን ለማከናወን ከUNEP 222,050 USD ማግኘት ተችሏል፡፡
- ከስፔን የትብብር ኢጀንሲ ጋር በጋራ ለሚተገበረውፕሮጀክት "Women, Coffee and Climate: Women's Empowerment For Socio-Ecological Resilience of Coffee Value Chain Against Climate Change in Ethiopia (DeSIRA Project)" ከአውሮፓ ህብረት የ100,000 USD የበጀት ድጋፍ የውል ስምምነት በመፈራረም ወደስራ ተገብቷል፡፡
- የዛፍ ዘር ስርዓትንና የዘር ምንጭ ልማትን ለማዘመን እና ቀጣይ የምርምር ስራዎችን ለማካሄድ፣ ከኖርዌይ መንግስት በICRAF/PATSPO በኩል ለተቋሙ ለአራት ዓመት 6.74 ሚሊየን USD ማግኘት ተችሏል፡፡
- ከREDD+ Imvestment program 21 ሚሊየን USD በጀት ድጋፍ የውል ስምምነት በመፈራረም ወደ ስራ ተገብቷል፡፡
- ከሚቺጋን እና ፍሎሪዳ ዩንቨርሲቲዎች 79200 USD ለምርምር ስራ ማግኘት ተችሏል፡፡
- በአጠቃላይ ከአጋር አካላት በተገኘ ድጋፍ 28,261,250.00 USD እና 421,870.00 ብር ማግኘት ተችሏል፡፡
- ለClimate Investment Fund (CIF) የ50 ሚሊየን USD የፕሮጀክት ሃሳብ አቅርበን አዎንታዊ ምላሽ የተገኘ ሲሆን ዝርዝር የፕሮጀክት ሰነዱ በመዘጋጀት ላይ ነው፡፡
- በደረቃማ አካባቢዎች የሚገኙ ደኖችን ለማልማት፣ ለመጠበቅና ጥቅም ላይ ለማዋል እና የህብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የሚያስችል ለ Global Climate Fund (GCF) የ50 ሚሊየን USD የፕሮጀክት ሃሳብ ተዘጋጅቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር ቀርቧል፡፡
- ለSwedish International Development Agency (SIDA) የ10 ሚሊየን USD የፕሮጀክት ሃሳብ ተዘጋጅቶ የቅበላ ጊዜን በመጠባበቅ ላይ ነው፡፡
- GEF ለClimate change, restoration, green legacy inititative best practice and socio-economics and environmental resilience ስራዎች 5 million USD የፕሮጀክት ሀሳብ ተዘጋጅቶ ለUNEP ተልኳል፡፡
- በRIP Phase II የ40 ሚሊየን USD ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ለ RNE የቀረበ ሲሆን ከሰኔ ወር 2023 እ.ኤ.አ በፊት የውል ስምምነት ሰነድ እንደሚፈረም ይጠበቃል፡፡

## የተገኘ ውጤት

- መንግስት ከሚመድበው መደበኛ በጀት ባሻገር ተጨማሪ ሀብት ማግኘት ተችሏል፡፡

## ግብ 4፡- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል

- በዘጠኝ ወር ውስጥ የታቀደ ባይኖርም በኦሮሚያ ክልል የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀት መጠን ለመቀነስ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚን የሚተገብረውን የደን ሴክተርን በማስተባበር፣ በመደገፍና በማስፈጸም በዚህ ሩብ ዓመት 355,600 ቶን CO2e መቀነስ ተችሏል፡፡
- በ"REDD+" ፕሮጀክት ስራ እንደ አዉሮፓ አቆጣጠር ከ 2007 እስከ 2017 ያለውን የመሬት አጠቃቀምና ሽፋን የሚያሳይ መረጃ ለኦሮሚያ ክልል በማዘጋጀት በሚመለከታቸው አካላት የማስገምገም ስራ ተሰርቷል፡፡
- በዘጠኝ ወር ውስጥ በአለም አቀፍ፤ አህጉራዊ እና ቀጠናዊ መድረኮች ላይ ተሳትፎ ለማድረግ ታቅዶ በሁለት መድረኮች ላይ ተሳትፎ የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ በእነዚህም መድረኮች የተከናወኑት ስራዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-
  - 1ኛ. ኒውዮርክ ላይ በተካሄደው የመንግስታቱ ድርጅትን 77ኛው የስብሰባ መድረክ ኢትዮጵያ በምክትል ጠ/ሚንስትር እና ውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ የሚመራ ልኡክ በስብሰባው ተካፍሏል፡፡ ኒውዮርክ በሚገኘው የኢትዮጵያ ሚሽን በተባበሩት መንግስታት አጠቃላይ ጉባኤ (UN general assembly) ላይ የጎንዮሽ መድረክ ተዘጋጅቶ ከተለያዩ ሀገራት የተውጣጡ ሀላፊዎች የልማት አጋር አካላት እና የሚዲያ አካላት በተገኙበት ምክትል ጠ/ሚ መድረኩን በንግግር ከፍተው አየመሩት የአረንጓዴ አሻራ የቴክኒክ ኮሚቴ አስተባባሪው የሀገራችንን የ4 አመታት የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ውጤታማ አፈፃፀም የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በተመለከተ የ5 ደቂቃ ቪዲዮ፣ ብሮሸርና ዝርዝር ሪፖርት በማቅረብ ለተሳታፊ ሀገራት ማሳወቅ ተችሏል፡፡ ኢትዮጵያ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን አጠናክራ የመቀጠልና የአየር ንብረት ለውጥ ችግርን ለመቅረፍ በስፋት እንደምትሰራና ይህን በጎ ጅማሬ ወደ ጎረቤት ሀገራትም እያሰፋች እንደሆነ ማስገንዘብ ተችሏል፡፡
  - 2ኛ. በ27ኛው ሻርም ኤል-ሼክ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ላይ በመሳተፍ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ ድርድር መድረኮች እና ፎረሞች ላይ በመሳተፍ የሀገራችንን ልምድ በማካፈል ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮች እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡

## የተገኘ ውጤት

- በደን ልማት፣ ሪስቶሬሽን እና የአረንጓዴ አሻራ ስራዎች ዙሪያ የልምድ ልውውጥ ተደርጓል፡፡

## ግብ 5፡- የደን ህግ ተከባሪነት ማጎልበት

- በዘጠኝ ወራት ውስጥ ሶስት የህግ ማዕቀፎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ 1065/2010 ማስፈፀሚያ ረቂቅ ደንብ በኢትዩጵያ ደን ልማት፣ የደንና ዱር እንስሳት ውጤቶች ገቢ ማሰባሰብያ

ቁጥጥር መመሪያ ( በኦሮሚያ ክልል) እና የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም መመሪያ ረቂቅ (በአማራ ክልል) የተዘጋጀ ሲሆን አፈጻጸሙ 100 % ነው፡፡

- የህብረተሰብ ግንዛቤ ከመፍጠር አኳያ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት 3 መድረኮች ለማዘጋጀት ታቅዶ ሃዋሳ እና አዲስ አበባ ከተሞች ላይ የኢትዮጵያ ደን ኢንዱስትሪዎች ተግዳሮቶች፣ መፍትሄዎቻቸውና መልካም አጋጣሚዎች ዙሪያ እንዲሁም ቦንጋ ከተማ ላይ ከፍትህ አካላት እና የሚመለከታቸው ባለድርሻአካላት ጋር በደን ህግ ተከባሪነት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ለማዘጋጀት የታቸለ ሲሆን አፈጻጸሙም 100 ነው፡፡
- በዘጠኝ ወራት ውስጥ በደን እንክብካቤና ጥበቃ ዙሪያ በአዋጆች፣ ደንቦችና የአሰራር መመሪያዎች ዙሪያ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ከማስፋት አንጻር ለ2 ሚሊዮን የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 2,836,640 (ከዚህ ውስጥ 1,075,456 ሴቶች) የማህበረሰብ ክፍሎች በህትመት፣ በተለያዩ ኤሌክተሮኒክስ ሚዲያዎችና መድረኮች ግንዛቤ ማስጨበጫ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነዉ፡፡
- በደቡብ ክልል፡- የማዘዋወርያ ፈቃድና ህጋዊ ደረሰኝ ሳይኖራቸዉ በህገወጥ መንገድ ሲዘዋወሩ ከተገኙ 1,904 ኩ/ል ከሰል፣ 20 ሜ/ኩ ግንዲላ፣ 268 ሜ/ኩ የማገዶ እንጨት ፣ እና 32 ሜ/ኩ ጣውላ ሽያጭ 910,000 ብር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡ እንዲሁም 83 ግለሰቦች (በስልጤ ዞን 41 አ/አደሮች፣ በጋሞ ዞን 42 አ/አደሮች) በደን ጭፍጨፋ ላይ ተሰማርተው በህግ ተጠያቂ የተደረጉ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 14 ግለሰቦች 2 ዓመትና 10,000 ብር ገንዘብ ተቀጥተዋል
- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፡- በክልሉ ቤንች ሸኮ ዞን በጉራ ፈርዳ ወረዳ በኢንቨስትመንት ስም ከተሰጣቸው መሬት በላይ ከተወረረው 603.971 ሄ/ር ውስጥ 185 ሄ/ር የደን መሬት በህግ አግባብ ተመላሽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ቀሪ የተወረሩ የደን መሬትን በፖሊስና ፍርድ ቤቶች በምርመራና ክስ ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡
- በአማራ ክልል፡- በህገ-ወጥ መንገድ ሲንቀሳቀስ የተያዙ 6,222 ኩንታል ከሰል እና 150 ጣዉላ፣ 61 ኩንታል ዕጣን (ነጭ 56 እና ጥቁር 5)፣ 56 ኩንታል ሙጫ፣ 4,601 ሜ/ኩ አጠና፣ 212 ሜ/ኩብ ማገር (የቆርቆሮና የግድግዳ)፣ 149 ሜ/ኩብ ግንዲላ፣ 155 ሜ/ኩብ ፍልጥ፣ 435 ሜ/ኩብ ማገዶ ውርስ ተደርጓል፡፡
- 44 የደን ኬላዎችን በአዲስ ማቋቋምና 191 ነባር ኬላዎችን ደግሞ የማጠናከር ሥራ ተሰርቷል፡፡ 39,046 የይለፍ ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡
- ጋምቤላ ክልል፡- በህገ-ወጥ የከሰል ስራ በተሰማሩ 39 ግለሰቦች ላይ ክስ ተመስርቷል፡፡ 372 ኩንታል ከሰል ተወርሶ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በህገ ወጥ ደን ዉጤቶች የማምረትና ግብይት ስራ ላይ በተስማሩ ባለሀብቶች በተደረገው የቁጥጥር ስራ ያለፈቃድ የሚሰሩ 18 እና ባለቤታቸው የማይታወቅ 13 በድምር 31 ህገወጥ ግለሰቦች የመለየት ሥራ የተሰራ ሲሆን በቀጣይ ህጋዊ እርምጃ ለመወሰድ ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡
- ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፡- የደን ግብረ ኃይል የማጠናከር ስራ ተሰርቷል፣ 13 የንግድ ፈቃድ እድሳት ተሰጥቷል፡፡
- ድሬደዋ ከተማ አስተዳደር፡- አንድ አዲስ ኬላ ተቋቁሟል፣ 830 ሸክም የማገዶ እንጨት ተወርሷል፡፡
- አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፡- 59 ይለፍ ፈቃድ ተሰጥቷል፣ 13 የንግድ ፈቃድ እድሳት ተሰጥቷል፡፡

- በዘጠኝ ወሩ በደን ውጤቶች ንግድ ለተሰማሩ 325 ግለሰቦች/ባለሀብቶች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ በኦሮሚያ 948 ግለሰቦች እና በአማራ 119 ሰዎች በድምሩ 1067 ግለሰቦች ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ሆኗል፡፡ አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ከዚህ በፊት በህገወጥ ሲሰሩ የነበሩን መመሪያዎችን በማሻሻል ህጋዊ ሆነው እንዲሰሩ በመደረጉ ነው፡፡
- በሌላ በኩል በአማራ ክልል ለ64 ሰዎች የደን ምርት ውጤቶችን የማምረት ፈቃድና ለ82 ሰዎች እድሳ እና ለ57 ድርጅቶች (28) እና ወጣቶች (29) በዕጣንና ሙጫ ማምረት ዙሪያ ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡

## የተገኙ ውጤቶች

- የህግ ተከባሪነት መሻሻል ታይቷል፡፡

## ግብ.6 - አገራዊ የደን ሽፋንን ማሳደግ

- የአገራዊ የደን ሽፋንን ለማሳደግ ይቻል ዘንድ 600,000 ሄ/ር የተከላ መሬት ለመለየት ታቅዶ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በተደረገው የመስክ ክትትልና ድጋፍ 748,000 ሄ/ር መለየት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ሆኗል፡፡
- የቀርቀሃ ደን ሽፋን 20,000 ሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 77,413.44 ሄ/ር ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ለቀርከሀ ልማት የተሰጠው ትኩረት ከፍተኛ በመሆኑና ከመደበኛ በተጨማሪ የፕሮጀክቶችና የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡
- 3 ቢሊዮን ደረጃቸውን የጠበቁ ችግኞች ተፈልተው እንዲተከሉ ለማድረግ ታቅዶ 3.415 ቢሊዮን ከ100% በላይ የደን ችግኞች መትከል ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ 48.383 ሚሊዮን የቀርከሀ ችግኝ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ 2,729,589 የደን ዛፍ ችግኞች በ1065.9 ሄ/ር ላይ የከፍታማ ቦታዎች የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ፕሮጀክት እና 2,761,808 የደን ችግኞች በ2384 ሄ/ር ላይ በደን ዘርፍ ትራንስፎርሙሽን ዩኒት የተተከሉ ናቸው፡፡ እንዲሁም በመስሪያ ቤታችንን ሰራተኞች በማንቀሳቀስ በመናገሻ ሱባ፣ በወንዶ ገነት፣ በአባይ ሸለቆ እና በደብረ ብርሃን ከተማ በጠቅላላው 23,500 ችግኞችን በ10.88 ሄ/ር ላይ የችግኝ ተከላ ማካሄድ ተችሏል፡፡

## ሠንጠረዥ 1 የክልሎችንና የከተማ አስተዳደሮች አፈጻጸም

| ክልል | የደን ችግኝ ተከላ | | ከተተከለው ጠቅላላ የደን ችግኝ ውስጥ የቀርከሀ ችግኝ ተከላ | | የችግኝ የጽደቀት መጠን በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የችግኝ ብዛት በሚ/ቁጥር | በተከላ የተሸፈነ የመሬት ስፋት በሄ/ር | የችግኝ ብዛት በሚ/ቁጥር | በተከላ የተሸፈነ የመሬት ስፋት በሄ/ር | |
| አማራ | 814.24 | 82,718.8 | 1.36 | 2,176 | 83.9 |
| ኦሮሚያ | 1866.95 | 437,066 | 22.23 | 35,568 | 91.8 |
| ደብብሕ | 458.88 | 165,897 | 4.2834 | 6,853.44 | 83 |
| ሲዳማ | 140.00 | 13,778.4 | 11.00 | 17,600 | 83.2 |
| ደ/ምዕ/ኢት | 99.92 | 26,472.79 | 1.38 | 2,208 | 84 |
| ቤ/ጉሙዝ | 29.00 | 20,294 | 8.00 | 12,800 | 85 |
| ጋምቤላ | 1.48 | 4,250 | 0.13 | 208 | 86 |
| አፋር | 1.94 | | | | 48 |
| ሶማሌ | 1.34 | 1,500 | | | 65 |
| ሐረሪ | 0.90 | 22 | | | 79.5 |
| ድሬዳዋ | 0.03 | 450 | | | 86 |
| **ድምር** | **3,414.68** | **748,198.99** | **48.383** | **77,413.44** | |
| **አማካይ** | | | | | **88.2** |

## ሠንጠረዥ 2 የፕሮጀክቶች ተሳትፎ በተከላ የተሸፈነ መሬት መጠን በሄ/ር

| የፕሮጀክቶች ተሳትፎ | በተከላ የተሸፈነ መሬት መጠን በሄ/ር |
|---|---|
| የደን ሴክተር አቅም ግንባታ ፕሮግራም FSDP | 31,968.83 |
| በደን ሴክተር ትራንስፎርሜሽን ዩኒት FSTU | 2,282.61 |
| በKFW ደን ልማትና ብዝሃ ሕይወት እንክብካቤ ፕሮጀክት | 745.9 |
| CRFL (የDANIDA ድጋፍ) ፕሮጀክት | 535.546 |
| በአውሮፓ ህብረት በሚደገፍ ፕሮጅክት | 2,575.63 |
| በከፍታማ ቦታዎች የአየር ንብረት ለዉጥ ማጣጣሚያ ፕሮጀክት | 1,065.9 |
| **ድምር** | **39,174.42** |

- የተተከሉ ችግኞችን የጽድቀት መጠንን ለማሳደግ ይቻል ዘንድ በኦሮሚያ 1,115,208.72ሄ/ር፣ አማራ 175,954.70ሄ/ር ሶማሌ 1,014 ሄ/ር፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች 369,802.00 ሄ/ር፣ ሲዳማ 11,068.00 ሄ/ር በድምሩ በ1,673,047.419 ሄ/ር መሬት ላይ (ከዚህ ውስጥ 11,330 ሄ/ር በደን ሴክተር አቅም ግንባታ ፕሮግራም የተከናወነ ነው) ለተተከሉ ችግኞች የተለያዩ የድህረ ተከላ የእንክብካቤ፣ የአረምና ኩትኳቶ እና አልፎ አልፎ ፍግ መጨመርና ውሃ የማጠጣት ስራ በተደረገው የመስክ ድጋፍና ክትትል ለማየት የተቻለ ሲሆን፣ የዓመቱ የመጀመሪያ ዙር የጽድቀት መጠን 85 በመቶ ለማሳደግ ታቅዶ ከአስር ክልሎች በተገኘው መረጃ መሰረት በአማካኝ 88.2 በመቶ የችግኝ የጽድቀት መጠን ተመዝግቧል፡፡

- የአረንጓዴ  አሻራ ስራዎችን በ5 ክልሎች (በኦሮሚያ፣አማራ፣ ደቡብ፤ ደቡብ ምዕራብ/ኢት እና ሲዳማ) የችግኝ ተከላ ያሉበትን ሁኔታ በተመረጡ ዞንና ወረዳዎች ናሙናዎችን በመውሰድ ድጋፍና ክትትል ተደርጓል። በዚህም
  - የተተከሉ ችግኞችና የመሬት ሽፋኑ ተመጣጣኝ መሆኑን፤
  - የተከላ ባለቤትነት ሁኔታ እና ከአላማ ጋር የተሳሰሩ መሆኑን፣
  - የተከላ ቦታዎቹ የጂፒኤስ መረጃ የተሰበሰበላቸውና ካርታ የተዘጋጀላቸው መሆኑን፣
  - በችግኝ ጣቢያ የተፈሉና የተሰራጩ ችግኞች ብዛት ከተተከሉ ችግኞች ጋር መጣጣማቸውን ማየት የመሳሰሉትን ተግባራት በመስክ ለማረጋገጥ ተችሏል።
- ለአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ለክትትልና ድጋፍ ስራ የሚውል ብር 10 ሚሊየን ከፍተኛ አፈፃፀም ለነበራቸው ሶስት ክልሎች ድጋፍ ተደርጓል።
- **የተጎዱና የተራቆቱ መሬቶች፡-** በዘጠኝ ወሩ 750,000 ሄ/ር የተጎዱና የተራቆቱ የደን መሬቶች ተለይተውና ተከልለው እንዲያገግሙ ለማድረግ ታቅዶ ሲዳማ 3,000 ሄ/ር፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ 3,892.9 ሄ/ር፣ ደቡብ 14,443 ሄ/ር፣ ሶማሌ 3,800 ሄ/ር፣ ኦሮሚያ 497,885 ሄ/ር (በልየታ ላይ ያለ) እና ጋምቤላ 2,300 ሄ/ር፣ አማራ 65,482.85 ሄ/ር፣ ቤ/ጉሙዝ 18,496 ሄ/ር በድምሩ 609,299.75 ሄ/ር ማከናወን ተችሏል። አፈፃፀሙም 81.2% ሆኗል። ከዚህ ውስጥ 18,976.52 ሄ/ር በደን ሴክተር አቅም ግንባታ ፕሮግራም የተከናወነ ነው።
- **የተከላ ቦታ ልየታ፡-** ለ2015 ዓ/ም በጀት ዓመት የችግኝ ተከላ ቦታ ልየታን በተመለከተ በዘጠኝ ወር ውስጥ የክልሎች አፈጻጸም ሪፖርት ሲዳማ 30,542 ሄ/ር ፤ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች 94,976 ሄ/ር፣ ድሬዳዋ 302 ሄ/ር አዲስ አበባ 95 ሄ/ር፤ ኦሮሚያ 410,404.8 ሄ/ር ፣አማራ 178,592 ሄ/ር፣ ጋምቤላ 2,496 ሄ/ር፣ ሶማሌ 1234.87 ሄ/ር፣ ደ/ምዕ/ኢትዮጵያ 1037 ሄ/ር በድምሩ 719,679 ሄ/ር ተለይቷል። ከዚህ ውስጥ 15,175 ሄ/ር በደን ሴክተር አቅም ግንባታ ፕሮግራም፣ 4036 ሄ/ር በKfW ፕሮጀክት የተከናወነ ሲሆን። ከተለየው የተከላ ቦታ ውስጥ 356,811ሄ/ር ለደን፣ 356,910 ሄ/ር ለጥምር ደን እርሻ እና 1333 ሄ/ር ለቀርሃ ችግኝ መትከያ የተዘጋጁ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ካርታ የተዘጋጀለት የተከላ ቦታ ስፋትም 157,028.98 ሄ/ር ነው።
- **የዛፍ ዘር ማሰባሰብና ስርጭት፡-** በዘጠኝ ወር ውስጥ 200 ቶን የዛፍ ዘር ለማሰባሰብና ለማሰራጨት ታቅዶ በአማራ 155.41 ቶን፣ በኦሮሚያ 802.95 ቶን፤ በደቡብ ብሔር በሔረሰቦችና ሕዝቦች 301.92 ቶን፣ ሲዳማ 12.77 ቶን፣ ድሬዳዋ 1.191 ቶን፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ 7.465 ቶን፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ 5.569 ቶን ዘር ማሰራጨት የተቻለ ሲሆን በድምሩ 1,287.275 ቶን ዘር ማሰራጨት ችለዋል። የተሰራጨው የደን ዘር በአይነት ሲታይ 516.729 ቶን የደን ዘር፣ 767.33 ቶን የጥምር እርሻ ደን ዘር፣ 3.216 ቶን የቀርከሃ ዘር ነው። በKFW ድጋፍ የደን ልማት ፕሮጀክት ለ9 የዛፍ ዝርያዎች 51 የዘር ምንጮች ተለይተዋል።
- **ፖሊቲን ቲዩብ አቅርቦት፡-** በዘጠኝ ወር ውስጥ በተመረጡ ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች መረጃ ሲታይ ኦሮሚያ 3250 ኩ/ል፤ አማራ 2,453 ኩ/ል፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች 1540 ኩ/ል፣ ሲዳማ 1429.6 ኩ/ል፣

ድሬዳዋ 39.71 ኩ/ል፣ ዴቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ 21.58 ኩ/ል እና ቤ/ጉሙዝ 89.35 ኩ/ል በድምሩ 8,822.93 ኩ/ል ማቅረብ ተችሏል፡፡

- **የችግኝ ጣቢያ ስራዎች፡-** በዘጠኝ ወር ውስጥ 112,553 ነባርና አዲስ ችግኝ ጣቢያዎች ወደ ስራ ማስገባት የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የክልሎች አፈጻጸም ሲታይ ኦሮሚያ 27,422፤ በአማራ 78,477፤ ደቡብ 6,236፤ ሲዳማ 323፤ጋምቤላ 95 ችግኝ ጣቢያዎች ናቸው፡፡ ከዚህ ውስጥ 224 ችግኝ ጣቢያዎች በደን ሴክተር አቅም ግንባታ ፕሮግራም የተከናወኑ ናቸው፡

- **ችግኝ ዝግጅትና ማፍላት፡-** የ2015 ዓ/ም በጀት ዓመት ችግኝ ዝግጅትና ማፍላትን በተመለከተ በዘጠኝ ወር ውስጥ 5.26236 ቢ/ን ችግኝ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ 3.46276 ቢ/ን ችግኞች በፕላስቲክ የተፈሉ ናቸው፡፡ የችግኝ ዝግጅቱ አፈጻጸም በአይነት 2.23217 ቢ/ን የደን ችግኝ፣ 3.022743 ቢ/ን ጥምር ደን እርሻ ችግኝ እና 8.728 ሚ/ን የቀርከሃ ችግኝ ናቸው፡፡ ለደን ከተዘጋጀው ችግኝ ውስጥ ለ2016 በጀት ዓመት ክረምት ተከላ የሚዉል ችግኝ የደን ሴክተር አቅም ግንባታ ፕሮጀክቱ በሚከናወንባቸዉ 58 ወረዳዎች በሚገኙ ቀበሌዎች እስካሁን በተካሄደዉ ቆጠራ 20.6 ሚ/ን ችግኝ ይሸፍናል፡፡

**ሠንጠረዥ 3 የችግኝ ማፍላት** (በቢ/ቁ) **የክልሎችንና የከተማ አስተዳደሮች አፈጻጸም**

| ክልል/ከተማ አስተዳደር | የደን ችግኝ በሚ/ን | ጥምር ደን-እርሻ ችግኝ በሚ/ን | የቀርከሃ ችግኝ በሚ/ን | ድምር | በፕላስቲክ የተዘጋጀ ችግኝ |
|---|---|---|---|---|---|
| አማራ | 395.000 | 110.000 | - | 504.000 | 210.000 |
| ኦሮሚያ | 1,325.000 | 2,798.000 | 7.900 | 4,130.000 | 2,980.000 |
| ደ/ብ/ብ/ሕ | 395.000 | 74.600 | 0.400 | 470.000 | 147.000 |
| ሲዳማ | 81.000 | 18.600 | - | 100.000 | 90.000 |
| ደ/ምዕ/ኢ.ት | 24.000 | 4.200 | - | 28.000 | - |
| ቤ/ጉሙዝ | 9.000 | 17.200 | 0.400 | 27.000 | 27.000 |
| ጋምቤላ | 0.600 | - | - | 0.600 | 6.000 |
| አፋር | 0.100 | - | - | 0.100 | 0.100 |
| ሶማሌ | 0.600 | - | - | 0.600 | 0.600 |
| ሐረሪ | 0.050 | - | - | 0.050 | 0.050 |
| ድሬዳዋ | 0.830 | 0.070 | 0.028 | 0.940 | 0.940 |
| አ/አ | 0.990 | 0.073 | - | 1.070 | 1.070 |
| **ጠቅላላ ድምር** | **2,232.170** | **3,022.743** | **8.728** | **5,262.360** | **3,462.760** |

- በዘጠኝ ወሩ በ4 ከተሞች ላይ የደን አያያዝ እንዲሻሻል ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ6 ከተሞች ማለትም (ባህርዳር፤ ሀዋሳ፤ ሰመራ፤ ጅማ፤ ደብረማርቆስ እና ቦንጋ) ከተሞች ድጋፍና ክትትል ተከናውኗል፡፡ በተለይም በተከላ ቦታ ልየታና ዝግጅት፤ በችግኝ ጣቢያ ውስጥ የሚከናወኑ ስራዎች አስመልክቶ ድጋፍና ክትትል

የተደረገ ሲሆን ክልሎችም በዚሁ አግባብ በተከላ ቦታ ዝግጅት፣ በተተከሉ ችግኞች እንክብካቤ (የአረምና ኩትኳቶ፣ ውሃ ማጠጣት) በሠው ሠራሽ ደን አያያዝ ስራዎችን አከናውነዋል፡፡

- በደቡብ ክልል የሶዶ ወረዳ፣ በሲዳማ ክልል በንሳና አሮሬሳ፤ በኦሮሚያ ክልል ቀርሳ፣ ደደርና አርሲ ሮቤ እንዲሁም በአማራ ክልል አንኮበርና የስማዳ ወረዳዎች ደን የተተከለባቸው እና በተፈጥሮ ያገገሙ ቦታዎችን የሚያሳይ የጂኦ ስፓሻል መረጃዎችን በዳታቤዝ የማደራጀት ስራ ተሰርቷል።
- በዘጠኝ ወራት ውስጥ የሁለተኛ ዙር ሀገራዊ የደን ሀብት ቆጠራ 40% ለማከናወን ታቅዶ የደን ቆጠራውን ለማካሄድ የሚያስፈልጉ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች 20% (ከአጠቃላይ ስራው) የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 50% ነው። አፈጻጸሙም ያነሰበት ምክንያት ስራውን በቴክኒክ የሚያግዘው የልማት አጋር ድርጅት ጋር በተያያዘ ችግር በተፈለገው መጠን ስራውን ማስኬድ ባለመቻሉ ነው። በዚህ ስር የተከናወኑ ስራዎችም የሚከተሉት ናቸው፡-
  - የደን ቆጠራ የመስክ ማኑዋል (Forest Inventory Field Manual) በአዲስ መልኩ ተዘጋጅቷል።
  - የመስክ መረጃ መሙያ ቅፅ (Field Form) ተዘጋጅቷል።
  - የደን ቆጠራውን (Forest Inventory) ለማከናወን የሚረዱ ወካይ ናሙናዎችን 714 ኮኦርዲኔቶች (Sample point XY Coordinates) ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ጂ አይ ኤስ ሶፍትዌር በመጠቀም ተዘጋጅተዋል።
  - በሀገር አቀፍ ሁለተኛ ዙር ደን ሀብት ጥናት ላይ ለሚሳተፉ ለ60 ባለሙያዎች በተግባር የተደገፈ ስልጠና ተሰጥቷል።

- በዘጠኝ ወራት ውስጥ የደን አያያዝ እቅድ ለ75,000 ሄክታር ደኖች የማኔጅመንት ፕላን እንዲዘጋጅና እንዲተገበር ለማድረግ ታቅዶ በኦሮሚያ ክልል 108,339 ሄ/ር የተፈጥሮ ደኖች፤ በአማራ ክልል ለ57,687.6 ሄ/ር ደኖች (45,200.5 ሄ/ር የተፈጥሮ ደን እና ለ12,487.1 ሄ/ር የሰው ሠራሽ ደን)፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ክልል 3047.85 ሄ/ር (2,571.85 የተፈጥሮ ደን እና 476 ሄ/ር የሰው ሰራሽ ደን) የደን መሬቶች በአጠቃላይ 169,074.45 ሄ/ር ደኖች የማኔጅመንት ፕላን የተዘጋጀ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው። ከዚህ ውስጥ 12,487.1 ሄ/ር በጂ.አይ.ዜድ ድጋፍ በአማራ ክልል የተዘጋጀ ነው።

- በዘጠኝ ወራት ውስጥ አንድ የደን ማኔጅመንት ፕላን Guideline /መመሪያ/ ለማዘጋጀት ታቅዶ በረቂቅ ደረጃ አንድ መመሪያ /Guideline ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን አፈጻፀሙ 100% ነው።
- በ19.2 ሚ/ሄ/ር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል ስራ ለማከናወን ታቅዶ በ18.68 ሚሊዮን ሄ/ር ደኖችን የመጠበቅ፣ የመንከባከብና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል የክትትልና ድጋፍ ስራ ተከናውኗል።
- በዘጠኝ ወራት ውስጥ የደን እሳት አደጋን ከመቆጣጠር አንጻር በርካታ ተግባራት ሲከናወኑ የቆዩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ፡-
  - በአምስት ክልሎች (ጋምቤላ፣ ቤ/ጉሙዝ፣ ደ/ብ/ብ/ህ፣ ኦሮሚያ እና አማራ) የደን እሳት አደጋ መከላከያ ብርጌድ ማጠናከር ተችሏል።

- በቤኒሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልል 846 ኪ/ሜ የእሳት መከላከያ መስመር ተሠርቷል፡፡
- በጋምቤላ ክልል አምስት የእሳት መቆጣጠሪያ ማማ ተሰርቷል፡፡
- በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልላዊ መንግስት የእሳት አደጋ ቁጥጥር ግብረ-ኃይል እስከ ቀበሌ ድረስ ማቋቋም ተችሏል፡፡
- የሰደድ እሳት የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓትን በመጠቀም በየሶስት ቀኑ የሚዘጋጀውን 75 የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ቡሌቲን በማመንጨት ክልሎችና ሌሎች በደን ላይ የሚሠሩ አካላት በኢሜይል እና በቴሌግራም እንዲደርሳቸው ተደርጓል፤ በዚህም የብሔራዊ ፓርኮቻች ተደረሽ ሆነዋል፡፡
- በአጠቃላይ በኦሮሚያ፣ በጋምቤላ እና በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልሎች የተከሰተውን የእሳት አደጋ ጉዳት እንዳያደርስ ከማድረግ አንፃር ከክልሎቹ ጋር በመቀናጀት እና በርካታ የማ/ሰብ ንቅናቄ በማድረግ ይደርስ የነበረዉን ከፍተኛ አደጋ መቀነስ ተችሏል፡፡
- የደን እሳት መንስኤዎችን መለየት፣ የቅድመ ማስጠንቀቂያና መከላከያ ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል አንድ የአሰራር መመሪያ ለማዘጋጀት ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተዘጋጅቷል፡፡
- ሶስት ጊዜ የደን እሳት ቃጠሎ ለመቆጣጠር እንዲቻል ግብረ ሃይል እንዲደራጅ እና እንዲጠናከር ክትትል እና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ሶስቱንም ጊዜ ማከናወን ተችሏል፡፡
- በአማራ ብ/ክ/መንግስት ለ461,066 ሰዎች በደን ሰደድ እሳት መከላከልና ቁጥጥር ላይ ግንዛቤ የመፍጠር ተግባር ተከናውኗል፡፡

- ማይዲዌትራ (MyDewetra) ፕላት ፎርም የተሰኘ የተፈጥሮ አደጋዎችን ክሰተት ለመከታተልና ለመተንበይ የሚያስችል ድረ-ገጽ በመጠቀም በደን ላይ ሊደርስ የሚችለውን የእሳት ቃጠሎ በተመለከተ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ዝርጋታ የሙከራ ትግበራ ማለትም የየእለቱን ምልከታና የየሶስት ቀኑ ትንበያ የድህረ ገፅ ዳሰሳ ማድረግ ተችሏል፡፡ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ በየሶስት ቀኑ የሚዘጋጀውን 56 ቡሌቲን በማመንጨት ክልሎችና ሌሎች በደን ላይ የሚሠሩ አካላት እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ የሚመነጨው የቅድመ ማስጠንቀቂያ ቡሌቲን መረጃው ለክልሎች እና ለብሔራዊ ፓርኮች እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡
- በዘጠኝ ወሩ መጤና ወራሪ አረምን አስመልክቶ የጎላ ችግር ባይኖርም፡-
  - በሲዳማ ክልል የታዩ መጤና ወራሪ አረምን ከመከላከል ረገድ  በ240 ሄ/ር ላይ የሚገኝ መጤና ወራሪ አረም በህብረተሰብ ተሳትፎ ማጽዳት ተችሏል፡፡
  - በኦሮሚያ ክልል በመናገሻ ሱባ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደን ውስጥ ተተክለው በሚገኑ የፓይነስ ፓቹላ ችግኞች ላይ የተከሰተውን የመድረቅ ምልክት መንስኤን የመለየት እና የመፍትሔ ሀሳብ የማቅረብ ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚሁ መሰረት የችግሩ መንስኤ ዶቲስትሮማ ኒድል ብላይት /Dothistroma needle blight/ በሚባል የወል ስሙ የሚታወቅ በሽታ ወይም በሳይንሳዊ መጠሪያ ስሙ Dothistroma septosporum በሚባል የተከሰተ ሲሆን በሽታው የጀመረው ከመርፌ ቅጠሎች /needles/ አናት ወደ ታች ሲሆን እነዚህ

መርፌ ቅጠሎች በሂደት ከአረንጓዴነት ወደ ቀይነት በመቀየር ችግኞቹ ሙሉ በሙሉ እንዲደርቁ የሚያደርግ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለተፈጠረው ችግር የመፍትሔ ሀሳቦችን በማመላከት ለኦሮሚያ ደንና የዱር እንስሳት ድርጅት በምስል የተደገፈ የመስክ ምልከታ ግብረ መልስ ማቅረብ ተችሏል፡፡

- የፀረ ፈንገስ መድሃኒቱ መዳብ /Copper/ ብረትን የያዘ ለምሳሌ Bordeaux mix እንዲሁም ክሎሮታሎኒል /Chlorothalonil/ እና ማንኮዜብ /Mancozeb/ የተባሉ መድሃኒቶችን አዲስ መርፌ ቅጠሎች በሚበቅሉበት የመጀመሪያ ወራት ውስጥ በመርጨት በዋነኝነት የበሽታው ስርጭትና ጉዳት መቀነስ ተችሏል፡፡
- የደን ሃብትን የሚያጠቁ የመጤ እና ወራሪ የዛፍ ዝርያ አረሞችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል አንድ ማንዋል ለማዘጋጀት ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተዘጋጅቷል፡፡
- ለደን ተባይ በሽታ ቅድመ መከላከል እና መቆጣጠር የሚያስችል አንድ ማንዋል ለማዘጋጀት ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተዘጋጅቷል፡፡
- በአጠቃላይ በዘጠኝ ወሩ የደን አደጋን ሊያስከትሉ በሚችሉ ስጋቶች ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ረገድ በተለይ እሳት፣ ተባይና በሽታ እንዲሁም መጤና ወራሪ የእጸዋት ተክሎችን በመለየት ሙያዊ ድጋፎችን በማከናወን እንዲሁም የመፍትሔ እርምጃዎችን በማስቀመጥ እና ግብረ መልስ በመስጠት የደን ሀብታችንን ከጉዳት በመታደግ የምርት መጠንና ጥራት እንዲጨምር የማድረግ ስራ ሲከናወን ቆይቷል፡፡

**የተገኙ ውጤቶች**

- ሃገራዊ የደን ሽፋን የማሳደግ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

**ግብ 7. የደን ሃብት ለኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተውን ጠቀሜታ ማሳደግ፣**

- በዘጠኝ ወሩ በ2.16 ሚ/ሄ/ር መሬት ላይ የሚገኙ እና በነባር የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት የታቀፈውን ደን በዘላቂነት እንዲጠበቁና ተገቢውን ግልጋሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ 2.16 ሚ/ሄ/ር 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ በመሆኑም:-
  - በኦሮሚያ በ792 በአሳታፊ ደን አስተዳደር ማህበራት ለተደራጁ ለ155,314 (ሴት 30,002)፣ በደ/ም/ ኢትዮጵያ በ422 ማህበራት ለተደራጁ ለ96,816 (ሴት 14,523)፣ በአማራ በ24 ማህበራት ለተደራጁ ለ4,338 (ሴት 867) በአጠቃላይ በ1,238 ማህበራት ለተደራጁ ለ256,468 (ሴት 45,392) የማህበሩ አባላት በበግና ፍየል ማደለብ፣ በዶሮ እርባታ፣ በዘመናዊ የንብ ቀፎ፣ እንጨት ነክ ባልሆኑ የደን ውጤቶች (NTFPs)፣ በማገዶ ቆጣቢ ምድጃ (Cook-stove)፣ በሶላር፣ በባዮጋዝ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡
- በዘጠኝ ወሩ 100,000 ሄ/ር አዲስ አሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ የተደረገለት የተፈጥሮ ደን ተገቢውን ጥቅምና አገልግሎት መስጠት እንዲችል ለማድረግ ታቅዶ 325,600 ሄ/ር (ከ100% በላይ) ማከናወን ተችሏል፡፡ በመሆኑም:-

- በኦሮሚያ  በ160,000 ሄ/ር ላይ ለተደራጁ 2 የአሳታፊ ደን አስተዳደር ማህበራት ለ163 (ሴት 3)፣ የማህበሩ አባላት
- በአማራ በ21,000 ሄ/ር ላይ በ8 ማህበራት ለተደራጁ ለ754 (ሴት 75) አባላት፣
- በደ/ም/ኢትዮጵያ በ24,600 ሄ/ር ላይ በ5 ማህበራት ለተደራጁ ለ1,551 (ሴት 113) አባላት፣
- በጋምቤላ ክልል 120,000 ሄ/ር ላይ በ18 ማህበራት ለተደራጁ ለ1465 (ሴት 500) አባላት፣
- በአጠቃላይ በ325,600 ሄ/ር ደን ላይ ለተደራጁ 33 የአሳታፊ ደን አስተዳደር ማህበራት ለ3,933 (ሴት 691) የማህበሩ አባላት ደኑን በዘላቂነት እንዲጠብቁና ጥቅም እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል፡፡

- በዘጠኝ ወር ውስጥ ለ220,000 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በደን ጥበቃ፤ የደን ምርቶችን በመጫን፤ በማጓጓዝና በማውረድ፤ በችግኝ ተከላና እንክብካቤ፤ በእንጨት ኢንዱስትሪ፤ ኢንተርፕራይዞች በመሰማራት፤ የደን ምርት ውጤቶችን በማቅረብ፤ በመቸርቸርና በመላክ፤ በከሰል ማክሰል(አማራ ክልል) እና የመሳሰሉት የስራ መስኮችን በአጠቃላይ ለ 259,920 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር የተቻለ ሲሆን አፈፃፀም ከ100% በላይ ነው፡፡ አፈፃፀሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በመንግስት፣ በህበረተሰቡ እና በሌሎች ባለድርሻ አካላት  ትኩረት በማግኘቱ እንዲሁም በግለሰቦች፤ በኢንተርፕራይዞች እና ኢንዱስተሪዎች በኩል የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ስራ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ በመምጣቱና የስራ ዕድል በመፈጠሩ ነው፡፡ ከተፈጠረው የስራ ዕድል ውስጥ በቋሚ የስራ ዕድል 32,660 (ወንድ 20,714 ሴት 11,946) ሲሆኑ ጊዚያዊ የስራ ዕድል ደግሞ 227,260 (ወንድ 151,958 ሴት 75,302) ናቸው፡፡

### ሠንጠረዥ 4. የክልሎች የተፈጠረ የስራ ዕድል አፈፃፀምን በተመለከተ

| ተ/ቁ | ክልል/ ከተማ አሰተዳደር | መለኪያ | የተፈጠረ የስራ ዕድል | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወ | ሴት | ድምር |
| 1 | ኦሮሚያ | ቁጥር | 15,475 | 8,815 | 24,290 |
| 2 | አማራ | ቁጥር | 112,264 | 57,995 | 170,259 |
| 3 | ደቡብ | ቁጥር | 41,144 | 17,569 | 58,713 |
| 4 | ሲዳማ | ቁጥር | 1,495 | 913 | 2,408 |
| 5 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | ቁጥር | 155 | 115 | 270 |
| 6 | ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ | ቁጥር | 1000 | 617 | 1,617 |
| 7 | አዲስ አባባ | ቁጥር | 734 | 996 | 1,730 |
| 8 | ድሬደዋ | ቁጥር | 405 | 228 | 633 |
| | **ድምር** | | **172,672** | **87,248** | **259,920** |

- በዘጠኝ ወሩ 180 ሚልዮን ብር ከሮያሊቲ እና ከተወረሱ የደን ምርት ውጤቶች ሽያጭ ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 246.6986 ሚልዮን ብር የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ አፈፃፀሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት የተሻለ ክትትልና ድጋፍ በመደረጉ እና ክልሎችም ትኩረት ስለሰጡት ነው፡፡

ሠንጠረዥ 5. የክልሎች ከሮያሊቲ እና ከተወረሱ የደን ምርት ውጤቶች ሽያጭ የተሰበሰበ ገቢ

| ተ/ቁጥር | ክልል/ ከተማ አስተዳደር | መለኪያ | ተሰበሰበ ብር መጠን | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከሮያሊቲ | ከቅጣትና ከደን ውጤቶች ውርስ ሽያጭ | ድምር |
| 1 | ኦሮሚያ | በሚሊዮን ብር | 46.7 | 8.7 | 55.4 |
| 2 | አማራ | በሚሊዮን ብር | 149.66 | 3.091 | 152.75 |
| 3 | ደቡብ | በሚሊዮን ብር | 29.161 | 0.91 | 30.071 |
| 4 | ሲዳማ | በሚሊዮን ብር | 5.34 | 0.2634 | 5.6035 |
| 5 | ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ | በሚሊዮን ብር | 0.845 | 0.09 | 0.935 |
| 6 | ቤንሻንጉል ጉምዝ | በሚሊዮን ብር | 0.819 | - | 0.819 |
| 7 | ጋምቤላ | በሚሊዮን ብር | 0.521 | - | 0.521 |
| 8 | አዲስ አበባ | በሚሊዮን ብር | 0.38 | - | 0.38 |
| 9 | ድሬደዋ | በሚሊዮን ብር | - | 0.218 | 0.218 |
| ድምር | | | 233.4266 | 13.272 | 246.6986 |

- በዘጠኝ ወሩ ከዘፍ ዘርና ከደን ተረፈ ምርቶች ሽያጭ 23.4 ሚ/ብር ማግኘት የተቻለ ሲሆን ይህም ገቢ የተገኘው የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ኢንተርፕራይዝ የዛፍ ዘር ማዕከሉን አጠናክሮ በማከነወኑ እና ገዥዎችም የዛፉን ጥቅም አውቀው ዘሩን በመግዛታቸው ምክንያት ነው፡፡
- ከሰው ሰራሽ ደንና ከደን ተረፈ ምርቶች በተሻሻለ ዘዴ የተመረተ ከሰልን በተመለከተ በዘጠኝ ወር ውስጥ 134,000 ቶን ለማቅረብ እቅድ ተይዞ ክንውን 219,000 ቶን የቀረበ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ አፈፃፀሙ ከፍ ያለበት ምክንያት የስራው አስፈላጊነት እየታመነበት ስለመጣ በከፍተኛ ሁኔታ ተመርቶ ለገበያ ስለቀረበ እና የገቢ ምንጭ በመሆኑ ነው፡፡
- በዘጠኝ ወሩ 680,000 ቶን የደን ምርት ውጤቶች ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በዕቅድ ተይዞ ክንውን 1,855,200 ቶን የቀረበ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ 15,196 ቶን ወደ ውጭ አገር የተላከ ምርት (አጠና፣ የተለያዩ ፈርኒቸሮች፣ የቀርከሀ ግንድ እና እጣንና ሙጫ) ነው፡፡ አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ከተሞች መስፋፋት ጋር ተያይዞ የግንባታዎች መስፋፋት፣ የደን ውጤት ለማህበረሰቡ እየሰጠ ያለው ጠቀሜታ እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የግንዛቤ ማደግ እና የክልሎችና የፌዴራል ክትትል እና ድጋፍ ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡
- በዘጠኝ ወሩ የደን ምርት ውጤቶችን ወደ ውጭ በመላክ የተገኘ እና በሃገር ውስጥ የደን ምርት ምክንያት የዳነ (Import Substitution) የውጭ ምንዛሪ መጠን 13 ሚሊዮን ዶላር ለማድረስ ታቅዶ 17.29 ሚሊየን ዶላር (ከ100% በላይ) ማግኘት የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 2.3977 ሚሊዮን ዶላር ወደ ውጭ ሀገር ከተላኩ የደን ውጤቶች የተገኘ ነው፡፡

- በዘጠኝ ወሩ ከደን ምርት ኤክስፖርት የተገኘ እና በሃገር ውስጥ የደን ምርት ምክንያት የዳነ (Import Substitution) የውጭ ምንዛሪ መጠን 13 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማድረስ ታቅዶ 17.29 ሚሊየን ( ከ100% በላይ ነው) ዶላር ማግኘት የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 2.397725 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወደ ውጭ ሀገር ከተለኩ የደን ውጤቶች የተገኘ ነው።

- በዘጠኝ ወሩ የደን ኢንተርፕራይዞች እና ኢንዱስትሪዎች በመስክ ክትትልና ድጋፍ 3 ጊዜ ለማድረግ ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል። በዚህም የክትትልና የድጋፍ ስራዎች የተለዩ ችግሮችን በተመለከተ የሃይል መቆራረጥ፤ የመለዋወጫ እጥረት፣ የገበያ ትስስር ችግር፣ የግብዓት አቅርቦት ዕጥረት እና የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን ለመለየት የተቻለ ሲሆን ችግሩን ለመቅረፍ ለገበያ ትስስሩና ለግብዓት አቅርቦቱ ችግር የጥሬ እቃ አቅራቢዎችንና የኢንዱስትሪ ባለቤቶችን የማገናኛ ሥራ ተሰርቷል። የሀይል መቆራረጥና የመለዋወጫ እጥረት ችግርን በተለመከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በወርክሾፕ ላይ ተነስቶ ውይይት ተደረጎበት ችግሩ እንዳለ ግንዛቤ እንዲፈጠር ተደርጓል።

**የተገኙ ውጤቶች፡-**

- ለዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል።
- ገቢ ማግኘት ተችሏል።

ግብ 8፡- የመረጃና ቴክኖሎጂ ማመንጨትና ማላመድ

በምርምር ስራዎች በዘጠኝ ወራት ውስጥ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተን እና የመሳሰሉት ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን በሂደት ላይ ያሉ ጠቅላላ 103 የምርምር ሙከራዎችን ተገቢው ክትትል እየተደረገላቸው ይገኛል።

## በሰው ሰራሽ ደን ምርምር የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- የማህበረሰቡን ጥምር ደን ግብርና እና የፍራፍሬ ዛፍ ፍላጎት የመለየት ጥናት መረጃ ወጥቷል። በዚህም መሠረት ሙዝ፣ ቡና፣ እንሰት፣ አቮካዶ እና ብርቱካን የመጀመሪያዎቹ አምስት ምርጫዎች እንድሆኑ ታውቋል።
- የማህበረሰብ የችግኝ ፍላጎትን በአይነት እና በመጠን የመለየት እና የችግኝ ጣቢያ አሰራር የሚያሳዩ 2 መረጃዎች ወጥቷል።
- የቀረሮ ዛፍ በቁርጥራጭ የሚባዛበትን ዘዴ የሚያሳይ መረጃ ወጥቷል።
    - መረጃውም በ0.2% IBA ሆርሞን የታከመው የችግኝ ቁርጥራጭ (seedling cuttings) ከ50 በመቶ በላይ ቀንበጥና ቅጠል እንዲሁም ስር የማብቀል ችሎታ አሳይቷል።
- በወንዝ ዳርቻ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥናት መረጃ ወጥቷል።
- በወንዝ ዳርቻ የሚገኙ የዛፍ እና የቁጥቋጦ ዝርያዎችን ስብጥር ጥናት መረጃ ወጥቷል።

- የነጭ ባህር ዛፍ የመትከያ ርቀት (በላይ ጋይንት የምርምር ሳይት) በእድገት መጠን ላይ ያለውን ተጽዕኖ ማወቅ የሚያስችል መረጃ ተሰብስቦ የሳይንሳዊ ትንታኔ እና የጽሁፍ ስራ ተጠናቋል። መረጃውም ወጥቷል።
  - የዛፍ የተከላ ርቀት እንደ አላማ የሚለያይ ቢሆንም አመላካች ውጤቱም፣ በአርባ ስምንት ወር የባህርዛፍ ዕድሜ በሰፊ የተከላ ርቀት ማለትም ሶስት ሜትር በ ሁለት ሜትር ተኩል የተተከለው የተሻለ ቁመትን (8.74 ሜ) ያሳየ ሲሆን በተቃራኒው ሶስት ሜትር በአንድ ሜትር ተኩል የተተከለው ዝቅተኛ (6.93 ሜ) ዕድገትን አሳይቷል። እንዲሁም በሁሉም የዕድሜ ደረጃዎች በሰፊ የተከላ ርቀት (3ሜ*2.5ሜ) ያለው የተሻለ ውፍረትም አሳይቷል።
- የኦሜድላ እና የዴክረንስ ግራር መሠረት ባደረገ የጥምር ደን ግብርና ሞዴል ላይ አንድ መረጃ ለማውጣት የአራት አመት መረጃ ትንታኔ የተሰራ ሲሆን በተጨማሪም የዚህ አመት አስፈላጊ የስብል ናሙና መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን መረጃው በአራተኛው ሩብ አመት ይወጣል።

## የዛፍ ዘር ምርምር ፕሮጀክት

- የበደኖ (Balanites aegyptiaca) ዘር የብቅለት ባህሪ ለማወቅ በተለያዩ ማከሚያ ዘዴዎች በመጠቀም የዘር ብቅለት ሙከራ እየተካሄደ ነው።
- የስር ቀስቃሽ ሆርሞኖች በመጠቀም ዝግባን በቁራጭ ለማባዛት የምርምር ናሙናዎቹን ለመሰብሰብ የእናት ዛፎች የሚገኙበትን ቦታዎች የመለየትና ቁራጮችን የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል።
- በኢላላ ጎጆ (ኦሮሚያ ክልል) ለተቋቋመው የፓይነስ ፓቹላ ዘመናዊ የዘር ምንጭ (ኦርቻርድ) የእድገት መረጃ እየተወሰደ ነው።
- በአምቢቂና ደገራ አቦ ሙከራ ጣብያ (አማራ ክልል) ላይ ያሉት የዴግሉፕታ ባህር ዛፍና የቶሩሎዛ ዝርያዎች የዘር ምንጭ ማቋቋም ሙከራዎች የክትትል፣ የሳይት ጽዳትና ተከስቶ የነበረውን ተባይ ማስወገድ ስራ ተሰርቷል።
- ከስፔን ሀገር የገባ የነጭ ባህር ዛፍ ዘር በእንጅባራ ኦርቻርድ ሙከራ ላይ መለያ ማድረግ፣ የክትትልና መረጃ መሰብሰብ ስራ እየተሰራ ይገኛል።

## የደን ተባይና በሽታ መከላከል ምርምር

- የፈረንጅ ፅድ ነፍሳተ ተባይ ቁጥጥርን (Cypress aphid) ስርጭት እና ጉዳት ለመቆጣጠርና ለመቀነስ ቀድመው የተለቀቁ የተፈጥሮ ጠላቶች (Wasps) ውጤት አስገኝተው የነበረ ሲሆን ነገር ግን በአሁኑ ስዓት ጥናቱ በሚከናወነበት አካባቢ በተደረገ የመስክ እና የላቦራቶሪ ክትትል እንደሌሉ በጥናት ተረጋግጧል። ስለሆነም እንደሃገር Cypress aphidን በዘላቂነት ለመቆጣጠር የተፈጥሮ ጠላቶች (Wasps) እንደገና ከውጭ በማስገባት ማራባት እና በስፋት መሰራጨት ያስፈልጋል።
- የቀርቀሃ ነፍሳተ ተባዮችን በተመለከተ በሲዳማ ክልል በተካሄዱ የመስክ የዳሰሳ ጥናቶች የተባይ የጉዳት ምልክቶች እንዳሉ የተረጋገጠ ሲሆን የተባይ ምልክት የሚታይባቸውን የቀርቀሀ ግንዶች በመስንጠቅ ጉዳት

አድራሽ ተባይ እንዳለ ታውቋል። የተባዩን የህይወት ዑደት (Life cycle) እና ዝርያ ለማወቅ ተባዩ የተገኘባቸዉ ግንዶችን ወደ ላቦራቶሪ በማምጣት የቤተ ሙከራ ክትትል እየተሰራ ይገኛል።

- የካቻ ግራርን (አኬሽያ ሚረንሲ) ነፍሳተ ተባዮችን እና በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር በተመለከተ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ እና በስፋት የተሰራጨው መጤ በሽታ ዝርያ (Uromycladium acaciae) ተለይቷል። መጤ በሽታው ከአዊ ዞን በተጨማሪ በጋሞ፣ በጉራጌ ዞኖች እና ሌሎች አካባቢዎች በስፋት ተከስቷል።በችግኝ ጣቢያዎች ደረጃ በሽታውን በኬሚካል ርጭት ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ተችሏል።
- በረጅም ጊዜ የመቆጣጠር እቅድ በሽታውን መቋቋም የሚችል 10 ኪ.ግ የአኬሽያ ዲከረንስ ዘር በማስገባት የችግኝ ጣቢያ ስራዎች ተጀምረዋል።

## በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ምርምር የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- የቴኩማኒ ፓይን እና የአኬሽያ ካፍራ የዛፍ ዝርያዎች ጣውላ አውዳሚ ተባዮችን የመቋቋም ባህሪ/አቅም የሚያሳይ የመስክ መረጃ የመሰብሰብ ስራ ተጠናቆ የተሰበሰበውም መረጃ ወደ ኮምፒዩተር የገባ ሲሆን የመረጃ ትንተና እየተካሄደ ይገኛል።
- ከቆላ ቀርከሃ ጣውላ (Laminated) ቴክኖሎጂ ለማውጣት የላብራቶሪ ናሙና  የተከናወነ ሲሆን የላቦራቶሪ ፍተሻ  ስራ እየተካሄደ ይገኛል።
- ከካማልዱለንስስ ባህርዛፍ እና ከአኬሽያ ዲከረንስ የወለል ንጣፍ (ፓርኬ) ማምረት የሚያስችል ቴክኖሎጂ ለማውጣት የሚረዳ ናሙና ዝግጅት የተከናወነ ሲሆን፣ ለላቦራቶሪ ፍተሻ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።
- የሁለት ዋና ዋና የዛፍ ዝርያዎች (የቀይ እና የነጭ ባህር ዛፍ) በተለያየ ስርአተ ምህዳር ያላቸውን የእምቅታ (Density) ባህርያት የሚያሳይ መረጃ ለማውጣት ናሙና ዝግጅት በማጠናቀቅ የላቦራቶሪ መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን የመረጃ ትንተና እየተከናወነ ይገኛል።
- ከሳሊግና ባህርዛፍ ተረፈ-ምርት ለኃይል ምንጭነት የሚውል ፒሌትና ብሪኬት ማምረት የሚያስችል ቴክኖሎጂ ለማውጣት የሚረዳ ናሙና ዝግጅት ተጠናቆ የላቦራቶሪ ፍተሻም በመከናወን ላይ ይገኛል።
- በብዛት ጥቅም ላይ ያልዋሉ የዕጣንና ሙጫ ዛፎች መለየት የሚያስችል ሙከራዎች ላይ የመስክ ምልከታና መረጃ የመሰብሰብ ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን የተሰበሰበውን መረጃ ወደ መረጃ ቋት የማስገባት ስራ እየተሰራ ይገኛል።
- የደጋ፣ የቆላ እና ከውጭ የገቡ የቀርከሃ ዝርያዎች የማላመድ ሙከራዎች ላይ የመስክ ምልከታና መረጃ የመሰብሰብ ስራዎች ተከናውነው፣ መረጃዎችንም ወደ መረጃ ቋት የማስገባት ስራ እየተሰራ ይገኛል።
- የዲማ (ባአባብ)፣ ጊሽጣ፣ የበረሃ ሎሚ፣ እንኮይና ሮቃን የማላመድ ሙከራዎች ላይ የመስክ ምልከታና መረጃ የመሰብሰብ ስራዎች ተከናውነው መረጃ ወደ መረጃ ቋት የማስገባት ስራ እየተሰራ ይገኛል።
- የሞሪንጋ ዛፍ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ያለውን የስርጭት እና የምርት መጠን ማወቅ የሚያስችል ሙከራዎች ላይ የመስክ መረጃ የመሰብሰብ እና የመተንተን ስራዎች ተከናውነዋል፤ የማጠቃልያ ሪፓርትም እየተዘጋጀ ይገኛል።

- የሞሪንጋ ዛፍ በተለያየ የቁመት መጠን የሚሰጠውን የምርት መጠን ማወቅ የሚያስችል ሙከራ ላይ የመስክ መረጃ የመሰብስብ እና መረጃ የመተንተን ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን የማጠቃለያ ሪፓርት የማዘጋጀት ስራም እየተሰራ ይገኛል፡፡

**የፖሊሲና ሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር**

- በመካከለኛ፤ በደቡብ እና ሰሜን ምህራብ ኢትዮጵያ አከባቢዎች የመሬት አጠቃቀም ከእርሻ ወደ ደን የሚቀየርበትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች የሚያሳይ መረጃ ተሰብስቦ፤ ተተንተኖ የመጀመሪያ ደረጃ ፅሁፍ ወጥቷል፡፡
- በመካከለኛው፤ በደቡብ እና ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ አከባቢዎች የመሬት አጠቃቀም ሽፋን ከደን ወደ እርሻ የሚቀየርበትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ምክንያት የሚያሳይ መረጃ ተሰብስቦ፤ተተንተኖ፤ ፅሁፍ ፅሁፍ እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡
- የእንጨት ኢንደስትሪዎችን ዉጤታማነትና ትርፋማነት ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ከተመረጡ አራት ከተሞች (አዲስ አበባ፣ ሃዋሳ፣ ጅማና ባህርዳር) ተሰብስቦ ለትንተና ወደ ኮምፒውተር ቋት ገብቶዋል፡፡
- ከዉጭ የገቡ የቀርከሃ ቴክኖሎጂዎች በማስተዋወቅ በተጠቃሚዎች ላይ የመጣዉን የዕዉቀት፣ የአመለካከት እና የፍላጎት ለዉጥ የሚያሳይ መረጃ በመሰብሰብ የትንተና ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

**የተፈጥሮ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ምርምር**

- በሶስት ተፈጥሮ ደን የተመረጡ ዛፍ ዝርያዎችን የአበባ እና የዘር ወቅት ጥናት መረጃ ተሰብስቦ ተጠናቋል፤ በሁለት ተፈጥሮ ደን ውስጥ የሚገኙ 10 የዛፍ ዝርያዎች የአበባ እና የፍሬ ወቅት መረጃ ወጥቷል፡፡
- በጉራጌ ዞን እኀ ወረዳ ውስጥ በሚገኘው የቆጠር ገደር የተፈጥሮ ደን የዕጽዋት አይነት እና ስብጥር የሚያሳይ መረጃ ወጥቷል፡፡
- የሁለት ዛፍ ዝርያዎች (ደደሆ እና የአጋም) የዘር ብቅለት መረጃ ወጥቷል፡፡
- ከሰል በማመረት ሂደት ውስጥ የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዝና ንጥረ ነገርን የሚያሳይ መረጃ ወጥቷል፡፡
- የአየር ንብረት ለውጥ በመጥፋት ላይ ባሉ የዛፍ ዝርያዎች እድገት ላይ ያለውን ጫና የሚያሳይ መረጃ ወጥቷል፡፡
- የመሬት አጠቃቀም የደን ይዞታን ለዉጥን የሚያሳይ ጥናት ለማጥናት የመሬት አጠቃቀም የደን ሽፋን ለዉጥን የሚያሳይ መረጃ መሰብሰብ፣ መረጃ ማስተያየት እና የመረጃ ትንተና ማድረግና ጽሑፍ መፃፍ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ መረጃው ወጥቷል፡፡
- ለማገዶ የሚሆኑ ጥናት የተደረገላቸው 4 የዛፍ ዝርያዎች ላይ ናሙና ተስብስቧል፡፡ የተሰበሰቡት ናሙናዎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቤተ ሙከራ ውስጥ ፍተሻ እንዲደረግባቸው ተልከዋል፡፡

- በተመረጡ የጣና ሀይቅ ዙርያ ቦታዎች ወደ ሀይቁ የሚገባውን የደለል መጠን ለመቀነስ የሚያስችል የመለያ ድንበር ዞን (buffer zone) ሙከራ ስራው ተለያዩ ችግኞችን በመትከል ስራው ተጀምሯል፡፡ ለተተከሉ እፅዋቶች የክትትል እና የጥበቃ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ የመጀመሪያ ዙር መረጃ ተሰብስቦ እየተተነተነ ይገኛል፡፡
- ወደ ጣና ሀይቅ የሚገቡትን ንጥረ-ነገሮች (nutrients) መጠን ሊቀንሱ የሚችሉ አገር በቀል ማክሮፋይትና ለአካባቢው ተስማሚና ፈጣን ዕድገት ያላቸውን ዛፎች መረጣና ልየታ የሚያሳይ መረጃ ለማውጣት ተመርጠው በ1500 ካሬ ሜትር ላይ ለተተከሉ ማክሮፋይቶች (ታይፋ፣ ኤለፋንት ግራስ፣ እና ፓፒረስ) የጥበቃ፣ የእድገት ሁኔታ የመከታተል እና የመንከባከብ ሥራ ተሰርቷል፡፡
- ወደ ዝዋይ ሀይቅ የሚገባውን ደለል ለመቀነስ የሚያስችል የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ምርምር ስራዎችን ተከናዉነዋል (2 ሄክታር መሬት ታጥሮ ለበፈር ዞን ተከላ የሚያገለግል ቦፈፌ የተባለ ዝርያ ተተክሏል፣ የአፈር እና የውሀ ጥበቃ ስራዎች ተሰርተዋል፣ ደለል ለመለካት የሚያስችሉ መሳሪያዎች ተተክለዋል)፣ ለተተከሉት የቦፈፌ ችግኞች እና የአፈር እና የውሀ ጥበቃ ስራዎች የጥበቃ እና የክትትል ስራዎች ተሰርተዋል፡፡
- በሶማሌ ክልል በፋፈን አካባቢ የወራሪ ዕጽዋት በተፈጥሮ ደን ውስጥ የሚገኙትን የዕጽዋት እና የእንስሳት መኖ ዝርያዎች አይነትና  እና ስብጥር ላይ ያለውን ተጽዕኖ የሚያሳይ መረጃ ለማውጣት የሚያስችል ምርምር ስራ በከፊል የተካሄደ ሲሆን በበጀት ዕጥረት ምክንያት ስራው አልተጠናቀቀም፡፡
- የተመረጡ የግራር ዝርያዎችን እድገት ከአየር ንብረት ጋር ያላቸዉን ዝምድና ለማጥናት የእንጨት ናሙና በመሰብሰብ፣ የማድረቅ እና የትንተና ስራ ተሰርቷል፡፡
- በተጎዳ መሬት ላይ ባዮቻርን በመጠቀም በችግኝ እድገት እና በአፈር ካርቦን መጠን ላይ ያለውን ፋይዳ ለማጥናት የአፈር ካርቦን ቅድመ ጥናት መረጃ ተሰብስቧል፡፡
- የበረሃማነት ለዉጥን ከደን ሽፋን ለዉጥ ጋር በማገናኘት ጥናት ለማጥናት ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች ተሰብስበው በመተንተን ላይ ናቸው፡፡
- የአየር ንብረት ለዉጥ በተለያዩ የቢሆንልኝ (scenarios) የወደፊትን የአየር ሁኔታ ከዕጽዋት ሽፋን ጋር ያለውን ግንኙነት ማሳየት የሚያስችል መረጃ ተሰብስቦ ለትንተና ዝግጁ ተደርጓል፡፡
- የእርጥበታማ ደኖች ለአየር ንብረት ለዉጥን ለመቋቋም ያላቸዉን አስተዋጽኦ የሚያሳይ መረጃ ተሰብስቦ ለትንተና ዝግጁ ተደርጓል፡፡

## ግብ 9. የመረጃና ቴክኖሎጂ ትውውቅና ሽግግርን ማሳደግ

## የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- በቴክኖሎጂ ቅድመ ማስፋፋት ስራ በአርሶ አደሮች ማሳ ላይ እየተላመደ ያለዉ ከዉጭ የገባዉ ቀርከሃ ዝሪያ የመስክ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በኤክስቴንሽንና በዘርፉ ተመራማሪዎች በኩል ለተሳታፊ አርሶ አደሮች ተከታታይ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ የተሰራ ሲሆን የቀርከሃ እንክብካቤና አያያዝ ከግዜ ወደ ግዜ መሻሻልን አሳይቷል፡፡

- በቴክኖሎጂ ቅድመ ማስፋፋት ስራ በአርሶ አደሮች ማሳ ላይ እየተላመደ ያለዉ ከዉጭ የገባዉ ቀርከሃ ዝሪያ የመስክ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የዘርፉን እምቅ አቅሞች ማሳየት የሚያስችሉ ከውጭ ምንዛሪ፣ ከስራ እድል ፈጠራ እና ከኢንዱስትሪ ግብአት አቅርቦት ጋር በተያያዘ ከሚያስገኙት ጥቅም አንጻር የተቀረጹት መልእክቶችን በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ በሸገር ሬዲዮ፣ በፋናቲቪ፣ በብስራት ሬዲዮ፣ ኢትዮ ኤፍ.ኤ.ም 107.9.፣ በአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን፣ ኦሮሚያ ብሮድካስቲንግ ኔትወርክ፣ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እና በኢዜአ ቀርበው ለማህበረሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡
- በዛፍ ዘር ብቅለት ባህሪ ላይ በምርምር የወጣ መረጃ ለአለም አቀፍ ሳይንሳዊ የህትመት መፅሄቶች ተልኳል፣
- በፖሊሲና ሶሺዮኢኮኖሚክስ 2፣ በሰዉ ሰራሽ ደን 4፣ በተፈጥሮ ደን እና አየር ንብረት ለውጥ መርምር 4፣ እና በደን ዉጤቶች ኢኖቬሽን ምርምር 1 በድምሩ 11 የምርምር ውጤቶችን በታወቁ ጆርናሎች ላይ ታትመዋል፡፡
- በ2013 እና በ2014 በጀት ዓመት በተከናወኑ የምርምር ስራዎች ማለትም በሰው ሰራሽ ደን 16፣ በፖሊሲና ሶሺዮኢኮኖሚክስ 6፣ በተፈጥሮ ደንና አየር ንብረት ለዉጥ ምርምር 14 በድምሩ 36 የምርምር ውጤቶች ለተጠቃሚዎች እንዲተዋወቁ ለማድረግ የጽሁፍ ስራው በመዘጋጀት ላይ ነው፡፡
- የምርምር ስራዎች በሚከናወኑባቸው አካባቢዎች ላይ ከባለድረሻ አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ስለሚሰራው የምርምር ስራ እና ጠቀሜታው ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፡፡
- ለሁለት ነባር የዛፍ ዝርያዎች (*ጎንጺ-Milicia excels እና ባኦባብ-Adansonia Digitata*) የአመራረት ማኑዋል በመፃፍ ላይ ነው፡፡
- ሁለት (*የአፈር ፊዚኮኬሚካል እና የልውጠ ህያዋን መመርመሪያ*) የላቦራቶሪ ማኑዋሎች ለህትመት ተዘጋጅተዋል፡፡
- ከዚህ በፊት መረጃቸው ወደ ዛፍ ዘር ምንጮች የመረጃ ፖርታል ቋት ያልገቡ 40 የዛፍ ዘር ምንጭ መረጃዎች ወደ መረጃ ፖርታል ቋት እንዲገቡ ተደርጓል፡፡
- አንድ የምርምር ዉጤት በአንድ የመፅሀፍ ምእራፍ (Book chapter) ማሳተም ተችሏል *(DOI: http://dx.doi.org/10.5772/intechopen.109796)*
- የተለያዩ የእንጨት ዝርያዎች ለረጅም ጊዜ አገልግሎት የሚሰጡበትን ቴክኖሎጂ ለተጠቃሚዎች ማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

## የተገኙ ውጤቶች

- 21 የወጡ የምርምር ውጤቶችን ለተጠቃሚዎች ለማስተዋወቅ የጽሁፍ ስራው በመዘጋጀት ላይ ነው፡፡
- 11 የምርምር ውጤቶችን በታወቁ ጆርናሎች ላይ ታትመዋል፡፡
- 5 ማንዋሎች ለህትመት ተዘጋጅተዋል፡፡

**ግብ10፡- የወጣቶችና የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማሳደግ**

**የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዘጠኝ ወሩ ለ53,500 ሴቶች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ76,870 የስራ እድል የተፈጠረ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡
- በዘጠኝ ወሩ ለ200,000 ወጣቶች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ 181,794 ወጣቶች የስራ እድል የተፈጠረ ሲሆን አፈፃፀሙ 90.9% ነው፡፡
- በመደበኛ ስራ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ለማቆየት ቀላል መንገዶች በተመለከተ፣ የሴቶች ትምህርት አስፈላጊነት እና ጥቅሞች ለቢሮ ሰራተኞች አስፈላጊ የሆኑ የሥራ ቅያች፣ ጊዜ አያያዝና አጠቃቀም፣ የግል እድገት እና ጥቅሞቹ ዙሪያ ለ180 ሴት ሰራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰቷል፡፡
- የአለም አቀፍ የሴቶች ቀን ወይም ማርች 8 በተለያዩ አስተማሪ ዝግጅቶች ተከብሯል፡፡

**የተገኙ ውጤቶች፡-**

- በዘርፉ ሴቶችና ወጣቶች የሥራ ዕድል በማግኘት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

**ግብ 11. የዘርፉን የመሰረተ ልማት ሽፋን ማሳደግ፣**

**የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የሁለት ላቦራቶሪዎች ግንባታ ሂደትን የመከታተል ድጋፍ የማድረግና የመቆጣጠር ሥራ ተሠርቷል፡፡ በዚህም መሰረት
- የB+G+5 ላብራቶሪ ኮምፕሌክስ ግንባታን 70% ለማድረስ ታቅዶ አሁን ግንበታው ያለበት ደረጃ 25.84% ነው፡፡ ለፕሮጀክቱ አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን ዋና ዋና ምክንያቶች በግንባታ ግብዓቶች ላይ ከፍተኛ የዋጋ ንረት መከሰቱና ይህም የተቋራጩን የመስራት አቅም መፈታተኑ፣ በግንባታ ግብዓቶች እጥረት ምክንያት የሥራ ተቋራጩ በተለይ ሲሚንቶና የአርማታ ብረቶችን በሚያስፈልገው ጊዜ እና መጠን ለሥራ ማቅረብ አለመቻሉ፤ በዋጋ ማስተካከያ/ማሻሻያ ጥያቄ ላይ አማካሪ ድርጅቱ የገበያ ጥናቱን አጠናቆ ማቅረብ ላይ በፍጥነት ምላሽ መሥጠት አለመቻሉ ናቸው፡፡
- የG+3 ላብራቶሪ ኮምፕሌክስ ግንባታ 80% ለማድረስ ታቅዶ አሁን ግንባታው ያለበት ደረጃ 45.47% ደርሷል፡፡ ለፕሮጀክቱ አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን ምክንያት በዲዛይንና ተያያዥ ምክንያቶች ላይ በሥራ ተቋራጩ ለሚነሱ የማሻሻያ ጥያቄዎች አማካሪ ድርጅቱ ወቅታዊ ምላሽ መሥጠት አለመቻሉ፤ በግንባታ ግብዓቶች ላይ የተፈጠረው ከፍተኛ የዋጋ ንረት ተቋራጩ የግንባታ ግብዓቶችን (በተለይ የፊኒሺንግ ዕቃዎችን) በጊዜው አቅርቦ ግንባታውን ማከናወን አለመቻሉ፤ በዋጋ ማስተካከያ/ማሻሻያ ጥያቄ ላይ አማካሪ ድርጅቱ የገበያ ጥናቱን አጠናቆ ማቅረብ ላይ በፍጥነት ምላሽ መሥጠት አለመቻሉ ናቸው፡፡
- በዋናው መ/ቤት ተገልጋይን መሰረት ያደረገ የ(LAN) ማስፋፊያ ስራ ተሰርቷል፡፡

- በዋናው መ/ቤት ለሚገኙ የIFMIS እና በማዕከላት ለሚገኙ የ(IBEX) ተጠቃሚ ክፍሎች፤ ሰርቨሮችን ተደራሽ ማድረግ ስራ ተሰርቷል።

**የተገኙ ውጤቶች፡-**

- የመሰረተ ልማት ስራዎች እየተጠናከረ መጥቷል።

**ግብ 12፡- የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ**

- የማዕከላት እና የዋናው መ/ቤት  አመራርና ሠራተኞች በመልካም ስነምግባር እሴቶች፣ በአመራር ሥነ-ምግባር እና በሞራል እሴት፣ በስራ ስነ-ምግባርና ቅሬታ አቀራረብ ዙሪያ ለ276 (149 ወንድ እና 127 ሴት) ተሳታፊዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል።
- መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በቅሬታ እና አቤቱታ አቀራረብና በመንግስት የአገልግሎት አሰጣጥ  ዙሪያ በዋናው መ/ቤት እና በማዕከላት ለ251 ሠራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል።
- በኤሌክትሮኒክ የመረጃ መሰብሰቢያ ቅፅ ዲዛይንና አጠቃቀም ላይ ለ13 ባለሙያዎች የሶስት ቀናት የአሰልጣኞች ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።
- ከፌዴራል እና ከክልሎች ለተውጣጡ 60 ባለሙያዎች የሁለተኛው ዙር ሀገር አቀፍ የደን ጥናት ተሳታፊዎች ለ12 ቀናት የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠና ተሰጥቷል።
- ለ 4  ተመራማሪዎች የ 2 ቀን በ R ሶፍትዌር  ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።
- በ Identification Options and Scenarios of Voluntary Commitments for Biodiversity in the Agriculture፣ Livestock and Forestry in the Bale Eco-region and Southwest National Forest Of Ethiopia፣ GIS and Remote Sensing፣ Agroforestry for People, Peace and Prosperity Mobilization of Forest Financing እና Overview of Forest Management Certification” በሚሉ አርዕስቶች ላይ ለ13 ባለሙያዎች (ሴት 2) ስልጠና እንዲወስዱ በማድረግ የመፈጸም አቅማቸውን ማሳደግ ተችሏል።
- ከInternational Union of Forest Research Organizations (IUFRO) ጋር በመተባበር በForest Landscape Restoration ዙሪያ ከዋናው መስሪያቤት፣ ከክልሎች እና ከሁለት ከተማ አስተዳደር እንዲሁም ከ6 አጋር ተቋማት የተወጣጡ ለ30 ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል።
- ከINBAR ጋር በመተባበር የደን ባላደራነት- forest stewardship council (FSC) certification on forest management) ዙሪያ ለ36 ባለሙያዎች እና የደን ውጤቶች እሴት ሰንሰለት ዙሪያ ለ29 ባለድርሻ አካላት ስልጠና ተሰጥቷል፤ በአጠቃላይ ለ65 ሰዎች ስልጠና መስጠት ተችሏል።
- በኔፓድ አዘጋጅነት ማላዊ ሀገር  በተዘጋጀ ዓመታዊ AFR100 ስብሰባ ላይ አንድ የመስሪያ ቤታችን ባለሙያ እና ሌሎች ከአጋር አካላት የተሳተፉ 2 ባለሙያዎች በድምሩ 3 ባለሙያዎች እንዲሁም በናይጀሪያ National Restoration Registry and Monitoring በሚል ርዕስ በተዘጋጀ ስልጠና ላይ ከመስሪያቤታችን 2 ባለሙያዎችና ከአጋር መስሪያቤቶች 2 በድምሩ 4 ባለሙያዎች እንዲሳተፉ ተደርጓል።

- ከምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የደን ምልከታ (East and Southern Africa Forest Observatory/OFESA/ ፕሮጀክት ጋር በመተባበር በ ጂ አይ ኤስና ሪሞት ሴንሲንግ ለ8 ባለሙያዎች የአቅም ክፍተትን መሰረት ያደረገ ቴክኒካል ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በICRAF/PATSPO በተዘጋጀው የተፈጥሮ ደን እና የዛፍ ዝሪያዎችን የመለየት እና ስርጭታቸውን የማወቅ ስልጠና ላይ አምስት ተመራማሪዎች ተሳትፈዋል፡፡
- ለሁለት ተመራማሪዎች እና አንድ ቴክኒክ ረዳት በደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሶስት ቀን ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- ለ13 (ሴት 3) ተማራማሪዎች የመሬት አጠቃቀምና አያየዝ (Land Use Optimization) ላይ በR ሶፍትዌር የተደገፈ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በጂአይ ኤስ እና በስታትስቲክ ለ14 ተመራማሪዎችና ለ31 ባለሙያዎች በድምሩ ለ45 ሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በKOICA ድጋፍ በSustainable Forest Management ለ20 (ሴት 2) ተሳታፊዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ለተቋሙ ሰራተኞች የICSMIS, IFMIS እና eGP የአጠቃቀም ስልጠናና የስራ ላይ ድጋፍ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡
- ከተለያዩ ሀገራት በበይነ መረብ (Virtual) በደን ሀብት ጥናትና በ GIS & RS የሚሰጡ የተለያዩ ዌቢናሮችን 12 ባለሙያዎችን በማሳተፍ መከታተል ተችሏል፡፡
- የደን እንክብካቤና ጥበቃ ከማሳለጥ አንጻር አምስት(5) ባለሙያዎች (4 ወንድ እና 1 ሴት) የአጭር ጊዜ ስልጠና አግኝተዋል፡፡
- የረጅም ጊዜ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ ተመራማሪዎች፣ የልማትና የአስተዳደር ዘርፍ ሰራተኞች በመጀመሪያ ዲግሪ 1 ወንድ፣ በሁለተኛ ዲግሪ 41 (33 ወንድ እና 8 ሴት)፣ በሶስተኛ ዲግሪ 25 (23 ወንድ እና 2 ሴት)፣ በጠቅላላ 67 (57 ወንድ እና 10 ሴት) ሲሆኑ ተገቢው ድጋፍና ክትትል እየተደረገላቸው ይገኛሉ፡፡ ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ስራ የተመለሱ ሰራተኞች ደግሞ 7 ( 5 ወንድ እና 2 ሴት) ናቸው፡፡

**የተገኘ ውጤት**

- የፈጻሚውንና የአስፈጻሚውን አቅም በማሳደግ የዘርፉን የተግባራት አፈጻም ማሻሻል ተችሏል፡፡

## 5. የተቋሙ የፋይናንስ/ በጀት አፈፃፀም

- በዘጠኝ ወራት ውስጥ ከተለቀቀው መደበኛ በጀት 156,883,455.35 ብር ውስጥ 149,260,186.11 ብር ጥቅም ላይ ለማዋል የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 95.1% ነው፡፡ በካፒታል በጀት ከተለቀቀው 55,220,000.00 ብር ውስጥ 33,667,491.38ብር ጥቅም ላይ ለማዋል የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 61% ነው፡፡ የካፒታል በጀት አፈፃፀሙም ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት የሁለት ላቦራቶሪዎች ግንባታ በመዘግየቱ ነው፡፡ የችግሩ መንስኤ በሃገር አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የግንባታ ማቴሪያል እጥረት እና ዋጋ ንረት በመከሰቱ ነው፡፡ ይህንም ችግር ለመፍታት ተቋሙ ከተቋራጭ ድርጅቶች እና አማካሪው ድርጅት እንዲሁም ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ጋር

ውይይት በማድረግ የዋጋ ማስተካካያ ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን በአዲሱ የዋጋ ስሌት መሠረት ተጨማሪ በጀት እንዲመደብልን ጥያቄ ለገንዘብ ሚኒስቴር ቀርቧል፡፡ አጠቃላይ የተቋሙ የመደበኛና ካፒታል በጀት አፈፃፀም 86.2% ሆኗል፡፡

**ሠንጠረዥ 6. የመደበኛና የካፒታል በጀት አፈፃፀም**

| የበጀት ዓይነት | ለ2015 የተፈቀደ | በ9 ወር የተለቀቀ | በ9 ወር ጥቅም ላይ የዋለ | አፈፃፀም ከተለቀቀው በ% |
|---|---|---|---|---|
| መደበኛ | 183,847,855.00 | 156,883,455.35 | 149,260,186.11 | 95.1 |
| ካፒታል | 130,000,000.00 | 55,220,000.00 | 33,667,491.38 | 61.0 |
| ድምር | 313,847,855.00 | 212,103,455.35 | 182,927,677.49 | 86.2 |

## 6. የተቋሙ የኦዲት ግኝት ምልከታ

### በዘጠኝ ወሩ ውስጥ የተከናወኑ የኦዲት ስራዎች

በተከናወኑ ኦዲቶች ሁሉ የበላይ አመራርን ያካተተ የኦዲት መውጫ ስብሰባ በማድረግ ባለፉ ስራዎች የተፈጠሩ ክፍተቶች እንዲታረሙና በቀጣይ ስራ ግልፅነት እንዲፈጠር የማድረግ ስራ ተሰርቷል፣ በማዕከላት በመገኘት የኢንስፔክሽንና ክትትል ስራዎች ተሰርቷል፣ የንብረትና ሂሳብ ምዝገባ ወቅታዊነት የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡ በፌደራል የክዋኔ እና የፋይናንስ ኦዲት ግኝቶችን መሰረት በማድረግ መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ ተገቢው ክትትል በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ጥረት ተደርጓል፡፡ የኦዲት ግኝቶችና የተወሰዱት የማስተካከያ እርምጃዎችም ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 8. የኦዲት ግኝቶችና የተወሰዱት የማስተካከያ እርምጃዎችም**

| ተ.ቁ | የኦዲት ግኝት | የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ |
|---|---|---|
| 1 | በተቋሙ 12 ዳይሬክተሮች የተከፈለ የኃላፊነት አበል ብር 440,000.00 | ሲከፈል የነበረው የኃላፊነት አበል ከግንቦት ወር 2014 ዓ.ም ጀምሮ እንዲቆም ተደርጓል፡፡ |
| | | በህጉ አግባብ ከመጋቢት ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ ተመላሽ እየተደረገ ይገኛል፡፡ |
| 2 | ከስራ ለለቀቁ ለለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ ብር 9,449.00 መኖሩ፣ | በፋይናንስ መመሪያው መሠረት ኮሚቴ ተቋቁሙ የማጣራት ስራ ተጀምሯል፡፡ |
| 3 | የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ወጪ ብር 2,530.00 በቢሮ ዕቃዎች መያዝ ሲገባው በመስተንግዶ ወጪ የተመዘገበ | አስተያቱን ተቀብለን በቀጣይ ተመሳሳይ ችግር እንዳይከሰት ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ ተስማምተናል፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| | መሆኑ፣ | |
| 4 | ለትምህርት በሀገር ውስጥና በውጭ ተምረው በውሉ መሠረት ወደ ስራ ያልተመለሱ ሰራተኞች መክፈል የሚጠበቅባቸው ብር 306,652.00 መኑሩ፣ | በፌዴራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት ገንዘቡ በሚፈለግባቸው በሶስት ግለሰቦች ላይ ክስ ተመስርቶ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ |
| 5 | ማስረጃ ያልቀረበበት ወይም በጥሬ ገንዘብ ተመላሽ ያልተደረገ ያልተወራረደ ሂሳብ ብር 385,313.74 መኖሩ፣ | ብር 356,662.74 በቀድሞው የአካባቢና ደን ምርምር ኢንስቲትዩት ትግራይ ማእከል የሚፈለግ ሲሆን ቀሪው ብር 28,651.00 ላይ ብር 1,980.47 ተመላሽ ተደርጎ ቀሪውን ተሰባሳቢ ሂሳብ በማጣራት የውሳኔ ሃሳብ እንዲቀርብ ኮሚቴ ተቋቁሞ የማጣራት ስራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ |
| 6 | ከአንድ ዓመት በላይ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ብር 2,019.05 መኖሩ፣ | ተገቢው ማጣራት ተደርጎ እርምጃ ለመውሰድ መርሃ ግብር ተዘጋጅቷል፡፡ |
| 7 | በዋና መ/ቤት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች መኖራቸው፣ | በንብረት አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት በቀጣይ እርምጃ ለመውሰድ በመርሃ ግብር ተይዞ እንዲከናውን አቅጣጫ ተሰጥቶበት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ |
| 8 | ከአቶ ብርሃኔ አሳየኸኝ የላፕቶፕ ሂሳብ ቀሪ ብር 11,687.00 የሚፈለግ መሆኑ፣ | ይህንኑ ለማጣራትና የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብ በተቋቋመው ኮሚቴ በመታየት ላይ ይገኛል፡፡ |
| 9 | በምርታመነት ማሻሻያ ልኬት ያልተከናወነላቸው ቀሪ 36 መኪናዎች መኖራቸው፣ | 36 መኪናዎች ምርታማነት ማሻሻያ ልኬት ለማከናወን ከሚመለከተው አካል ጋር ግንኙነት ተጀምሮ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ |
| 10 | የባለቤትነት ማረጋገጫ በኢትዮጵያ ደን ልማት ስም ያልተቀየረላቸው 38 መኪናዎች መኖራቸው፣ | የባለቤትነት ማረጋገጫ በተቋማችን ስም እንዲቀየር አስፈላጊውን መረጃ አቅርበን መረጃውን በመረከብ ሂደት ላይ እንገኛለን፡፡ |

## 7. ተቋማዊ ለውጥና የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም

- የ2014 በጀት አመት የመ/ቤቱ የእቅድ አፈጻጸም የዋናው መ/ቤት እና ማእከላት አመራሮች፣ እንዲሁም መላው ሰራተኛ በተሳተፉበት መድረኮች ግምገማ ተካሂዶ የበለጠ መጠናከር በሚያስልፈጋቸው ጉዳዮች ዙሪያ ላይ ግብአት ተወስዷል፡፡
- የ2015 በጀት አመት የተቋሙ እቅድ አሳታፊ በሆነ መንገድ ተዘጋጅቶ የዋናው መ/ቤት እና ማእከላት አመራሮች፣ ከተገመገመ በኂላ ለመላው ሰራተኞች እንዲሁም ለክልል ባለድርሻአካላት እንዲተዋወቅ ተደርጓል፡፡
- የ2015 በጀት አመት የየሩብ ዓመት አፈፃፀም በተቋሙ ማኔጅመንት አባላትና አመራሮች፣ ከመላው ሰራተኛውና ከክልሎች ጋር በጋራ ግምገማ ተካሂዷል፡፡

- የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓትን ለማጠናከር የቅሬታ እና አቤቱታ ማቅረቢያ ቅጾች ተዘጋጅተው አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ስራ ተገብቷል፣
- የሰራተኞች የስድስት ወር የዉጤት ተኮር ግምገማና ምዘና ውጤት በወቅቱ ተጠቃሎ እንዲገባ ክትትል ተደርጓል፡፡
- የፈጣን ለውጥ አምጪ መሳሪያዎችን በተለይም አቅጣጫ ጠቋሚዎች እንዲሟሉ ማድረግ ስራ ተከናውኗል፤
- ከሰራተኞች የቀረቡ  ቅሬታዎች በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ታይተው መልስ ተሰጥቶበታል፡፡
- ተቋማዊ የለውጥ ስራዎችን አስመልክቶ አንድ የልምድ ልውውጥ ተካሂዷል፡፡
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ 1263/2014 መሰረት የኢትዮጵያ ደን ልማት እራሱን የቻለ ህጋዊ ተቋም ሆኖ በአዋጅ 505/2014 የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነት ለመፈፀም ይረዳው ዘንድ መዋቅር በማዘጋጀት በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በፀደቁ የስራ መደቦች ላይ የሰራተኛ ድልድል እየተካሄደ ይገኛል፡፡

## 8. የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች አፈጻጸም

- በዋግ ህምራ መስተዳድር ሰቆጣና አካባቢው ተፈናቅለው ለሚገኙ የንብረት መዉደም አደጋ ላጋጠማቸውና በመጠለያ ጣቢያ ለሚገኙ ዜጎች 32 ኩንታል የዳቦ ዱቄት በብር 176,700.00 (አንድ መቶ ሰባ ስድስት ሺ ሰባት መቶ ብር)፣ ከሰራተኞች የተሰበሰበው 13 ኩንታል አልባሳት፣ 192 መመገቢያ ሳህንና 89 የመጠጫ ኩባያ፣ 1 ኩንታል ጫማ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ከአልማ ጽ/ቤት መጋዘን ተሰብስበው የተቀመጡ የተለያዩ ድጋፎች ማለትም 13 ቦንዳ ብርድ ልብስ፣ 10 ከረጢት መኮረኒ እና 20 ኩንታል የተለያዩ አልባሳት በመረከብና በመጫን በአጠቃላይ በዋግ ህምራ መስተዳድር ሰቆጣና አካባቢው ግምቱ ከ400,000.00 (አራት መቶ ሺ ብር) በላይ የሆነ ቁሳቁስ አስረክበናል፡፡
- ለሀገር መከላከያ ሰራዊት ከመ/ቤቱ አመራሮችና ሰራተኞች የገንዘብ ድጋፍ በመሰብሰብ ብር 432,500.00 /አራት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ አምስት መቶ/ በማዋጣት 80 ኩንታል የዳቦ ዱቄት በመግዛት እና ከአመታዊ በጀታችን 3.2 ሚሊዮን ብር  ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ለአቅመ ደካሞች ለበዓል መዋያ 168 ሌትር ዘይት ከተቋሙ ሠራተኞች ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- በአማራ ክልል በተለያዩ ወረዳዎች በጦርነት ለተጎዱ አካባቢዎች 60,059.00 ዶላር እና 929,766.00 ብር የሚገመት የቢሮና የመስክ ቁሳቁስ (GPS map, Compass, Clinometer, Caliper, LCD projector, Printer, Desktop, Highbar Chair, Metal Shelf, Expert table, Managerial cabinet, እና ሌሎች የቢሮ እቃዎች፣ እና የመስክ መሳሪዎች) ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ለማዕከላትና ደን ላይ ለሚሰሩ የክልል ተቋማት የማስፈጸም አቅም ለማጎልበት ተሽከርካሪ (9 መኪና ማለትም 2 Toyota Land Cruser Hard Top እና 7 Toyota Land Cruser Double Pick Up እና 12 ሞተር ሳይክል) እንዲሁም 307,773.81 ዶላር እና 905,297.38 ብር የሚያወጣ የቢሮና የመስክ መሳሪያዎች፣ (ሶላር ፓኔል፣

GPS map, Compass, Clinometer, Caliper, Cannon,LCD projector, Printer, Desktop, Laptop, Highbar Chair, Metal Shelf, Expert table, Managerial cabinet, Sensitive electric babalce, እና ሌሎች የቢሮ እቃዎች፣ እና የመስክ መሳሪዎች) ድጋፍ ተደርጓል፡፡

## 9. የዋና ዋና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም

- የደን ዉጤቶች ኢኖቬሽን ላቦራቶሪ ኮምፕሌክስ G+3 ህንፃ ግንባታ ስራው 45.13 ፐርሰንት ላይ መድረስ ተችሏል፡፡
- የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ማዕከል ላቦራቶሪ ኮምፕክስ B+G+5 ህንፃ ግንባታ ያለበት ደረጃ 25.71 ፐርሰንት ላይ ነው፡፡

## 10.የዕቅድ አፈጻጸም ክትትል እና ግምገማ ሥራዎች

የ2014 በጀት ዓመት የስራ አፈፃፀም ግምገማ በዋናው መስሪያ ቤትና በማዕከላት ተካሄዶ በተወሰደው ግብዓት የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ በቢኤስ ሲ መሰረት ተዘጋጅቶና ከመላው ሰራተኞች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ከተገመገመ በኋላ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በዝግጅት ምዕራፍ በልማት፣ በምርምሩ እና በአስተዳደር ዘርፍ በዕቅዱ መሰረት ስራዎች መከናወናቸውን በየስራ ክፍሉ በመስክ ምልከታ፣ በስልክ፣ በኢሜል እና በሪፖርት የመረጃ ልውውጥ በማድረግ እንዲሁም በጋራ መድረክ የአፈፃፀም ግምገማ በማካሄድ አፈፃጸም መከታተል ተችሏል፡፡ የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በመስክ ተገኝተው የሰጡትን ምክረ ሃሳብ እንዲሁም በፅሁፍ የሰጡትን ግብረ መልስ በግብዓትነት በመጠቀም አፈፃፀምን ማሻሻል ተችሏል፡፡

## 11.በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተወሰዱ/ሊወሰድ የሚገባቸው የመፍትሔ እርምጃዎች ተግዳሮቶች

- የተሟላ ሪፖርት ከክልሎች በወቅቱና ጥራት ባለው ደረጃ ማግኘት አለመቻል፣
- የፀጥታ ችግር፣
- በግንባታ ዕቃዎች ዕጥረትና ዋጋ መናር ምክንያት ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ መጠናቀቅ አለመቻላቸው፡፡
- የበጀት ዕጥረት
- የዋጋ ንረት ያስከተለው የኑሮ ውድነት በመስክ ስራዎች ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ

### የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- ሪፖርት በወቅቱና በሚፈለገው ጥራት እንዲያቀርቡ ከክልሎች ጋር ውይይት የተደረገ ሲሆን በመሰረታዊነት ችግሩ አልተፈታም፡፡

- ከግንባታ ተቋራጭ ድርጅቶቹ ሃላፊዎች፣ ከአማካሪው ድርጅት አመራሮች፣ ከግንባታ ቁጥጥር ባለስልጣን ባለሙያዎች፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን አመራሮች ጋር በመነጋገር የዋጋ ለውጥ በግንባታ ላይ ያስከተለውን ችግር እንዴት መቅረፍ እንደሚቻል ውይይት ተደርጓል፡፡ ለመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ በቀጣይ የግንባታው ስራ እንዲፋጠን ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡
- ያለውን በጀት በቁጠባ በመጠቀም ተጨማሪ በጀት እንዲፈቀድልን ለገንዘብ ሚኒስቴር ጥያቄ ቀርቧል፡፡

## 12. ማጠቃለያ

በበጀት ዓመቱ የሚጠበቁ ውጤቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፈፀም እንዲያስችል የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎችን በማከናወንና ለስራው አስፈላጊ ግብዓቶችን በማሟላት በባለፉት ዘጠኝ ወራት የታቀዱ ተግባራት በውጤታማነት ማከናወን የተቻለ ሲሆን አዲሱን የተቋም አደረጃጀት ተከትሎ በመሰራት ላይ ያለውን የመስሪያ ቤቱን መዋቅር ከዳር ለማድረስ አመራሩ እና ፈፃሚው በጋራ ተረባርቦ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ስለሆነም የዘጠኝ ወሩ የፊዚካል ስራ አፈፃፀም 95.8% እንዲሁም የበጀት አፈፃፀሙ 86.2% በመቶ ሆኗል፡፡ በቀጣይ ቀሪ ስራዎችን በዕቅዱ መሰረት በውጤታማነት ለመፈፀም እና የተሻለ አፈፃፀም ለማስመዝገብ ጠንክሮ መስራት ይጠበቃል፡፡

## 13.አባሪ

## አባሪ አንድ ፡- የ2015 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር አፈጻጸም ሪፖርት በቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 ኢላማ | የ3ኛ ሩብ ዓመት | | | ሪፖርቱ እስከሚሸፍነው ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% |
| ተገልጋይ | **ግብ 1. የተገልጋዮች እርካታን ማሳደግ** | | | | | | | | | |
| | ያደገ የተገልጋይ እርካታ | በመቶኛ | 84 | 90 | 88 | | | 86 | 84 | 97.6 |
| | በአገልግሎት አሰጣጥ ለሚነሱ ቅሬታዎች የተሰጠ ምላሽ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ፋይናንስ | **ግብ 2. የሀብት አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማሳደግ** | | | | | | | | | |
| | ጥቅም ላይ የዋለ በጀት ድርሻ | በመቶኛ | | 100 | 100 | 86.2 | 86.2 | 100 | 86.2 | 86.2 |
| | በኦዲት ግኝት ላይ የተወሰደ ማስተካከያ እርምጃ | በመቶኛ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | የተደረገ የውስጥ ኦዲት ክትትል | በቁጥር | 4 | 4 | 1 | 1 | 100 | 3 | 3 | 100 |
| | የኦዲት ግኝቶች መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ የማስተካከያ መርሃ ግብር | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 100 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| | **ግብ 3. የሀብት ግኝትን ማሳደግ** | | | | | | | | | |
| | ከአጋር ሀገሮች እና ድርጅቶች የተገኘ የፋይናንስ ድጋፍ | በሚሊየን ዶላር | | 30 | 10 | - | - | 30 | 28.22 | 94.06 |
| | ከዛፍ ዘርና ተረፈ ምርት ሽያጭ የተገኘ ገቢ | በሚ/ብር | 0.78 | 1 | 0.4 | 0.16187 | 40.5 | 0.9 | 23.562 | 100 |
| የውስጥ አሰራር | **ግብ4. ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል** | | | | | | | | | |
| | ከደን ዘርፍ የተቀነሰ የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀት መጠን | በሚ/ቶን | 10.2 | 7 | | | | | 0.3556 | |
| | ተሳትፎ የተደረገባቸው አለም አቀፍ አህጉራዊ እና ቀጠናዊ መድረኮች | ቁጥር | 2 | 2 | | | | 1 | 2 | 100 |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 ኢላማ | የ3ኛ ሩብ ዓመት | | | ሪፖርቱ እስከሚሸፍነው ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% |
| | **ግብ 5. የደን ህግ ተከባሪነት ማረጋገጥ** | | | | | | | | | |
| | የተዘጋጁ የደን ህግ ማዕቀፎች | በቁጥር | - | 4 | 2 | 2 | 100 | 3 | 3 | 100 |
| | ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ለመፍጠር የተዘጋጁ መድረኮች | በቁጥር | - | 3 | 2 | 2 | 100 | 3 | 3 | 100 |
| | በደን ህጎች እና አፈፃፀም ላይ ግንዛቤ ያገኙ የህብረተሰብ ክፍል ብዛት፣ | በሚሊዮን ቁጥር | 2.1 | 2.5 | 2 | 2.84 | 100 | 2 | 2.84 | 100 |
| | የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው በደን ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ብዛት | በቁጥር | 100 | 400 | 125 | 821 | 100 | 325 | 1067 | 100 |
| | **ግብ 6. አገራዊ የደን ሽፋንን ማሳደግ ፣** | | | | | | | | | |
| | ለተጠቃሚዎች የተሰራጨ የዛፍ ዘር መጠን | በቶን | 504.8 | 200 | 50 | 223.6 | 100 | 200 | 1,287.3 | 100 |
| | ወደ ዛፍ ዘር ስርዓት ያልገቡ እና ዕጥረት ያለባቸው ወደ ዛፍ ስርዓት የቀረቡ የዛፍ ዝርያዎች ብዛት | ቁጥር | | 15 | 5 | 1 | 20 | 13 | 9 | 69.2 |
| | የተዘጋጁ ችግኞች ብዛት | ቁጥር (በቢሊዮን) | **3.79** | 3 | 1 | 1.889 | 100 | 1.25 | 5.26 | 100 |
| | የተጠበቀ ነባር፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ደን መሬት ስፋት | ሄ/ር (በሚሊዮን ) | 19.2 | 19.2 | 19.2 | 18.68 | 97.3 | 19.2 | 18.68 | 97.3 |
| | የተተከሉ ችግኞች አማካይ የፅደቀት ምጣኔ | በመቶኛ | 83.5 | 85 | | | | 85 | 88.2 | 100 |
| | የዛፍ ተከላ የተካሄደበት መሬት ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | 0.699 | 0.6 | | | | 0.6 | 0.748 | 100 |
| | እንዲያገግም የተደረገ የተራቆተ የደን መሬት ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | 0.692 | 1 | 0.5 | 0.018 | 3.6 | 0.75 | 0.609 | 81.2 |
| | በቀርከሀ ደን እንዲለማ የተደረገ መሬት ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | 0.067 | 0.02 | | | | 0.02 | 0.077 | 100 |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 ኢላማ | የ3ኛ ሩብ ዓመት | | | ሪፖርቱ እስከሚሸፍነው ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% |
| | ለደን ሀብት ቆጠራ (Forest inventory) የተወሰደ ናሙና | በመቶኛ | - | 50 | 30 | 10 | 33.3 | 40 | 20 | 50 |
| | የደን ማኔጅመንት ፕላን የተዘጋጀላቸው ደኖች ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | 0.194 | 0.2 | 0.075 | 0.169 | 100 | 0.075 | 0.169 | 100 |
| | የደን አያያዝ የተሻሻለላቸው የከተሞች ብዛት | በቁጥር | 9 | 5 | 1 | 2 | 100 | 4 | 6 | 100 |
| | የጥምር ደን ግብርና ስራ እንዲጎለብት የተደረገበት የመሬት ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | | 0.1 | | 0.2982 | | | 0.3569 | |
| | የደን እሳት መንስኤዎችን መለየት፣ የቅድመ ማስጠንቀቂያና መከላከያ ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል ማንዋል | በቁጥር | | 2 | | | | 1 | 1 | 100 |
| | የደን እሳት ቃጠሎ ለመቆጣጠር እንዲቻል ግብረ ሃይል እንዲደራጅ እና እንዲጠናከር የተደረገ ክትትል እና ድጋፍ | በቁጥር | | 4 | 1 | 1 | 100 | 3 | 3 | 100 |
| | የደን ሃብትን የሚያጠቁ የመጤ እና ወራሪ የዛፍ ዝርያ አረሞችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የተዘጋጀ ማንዋል | በቁጥር | | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| | ለደን ተባይ በሽታ ቅድመ መከላከል እና መቆጣጠር የተዘጋጀ ማንዋል | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | 1 | 100 |
| | የተዘጋጀ የደን ማኔጅመንት ፕላን መመሪያ (Guideline) | በቁጥር | | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| | **ግብ 7. የደን ልማት ለአገራዊ የኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተውን ድርሻ ማሳደግ፣** | | | | | | | | | |
| | ነባር የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ የተደረገለት የተፈጥሮ ደን ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | 2.16 | 2.16 | 2.16 | 2.16 | 100 | 2.16 | 2.16 | 100 |
| | አዲስ የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ የተደረገለት የተፈጥሮ ደን ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | - | 0.2 | 0.1 | 0.2731 | 100 | 0.1 | 0.3256 | 100 |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 ኢላማ | የ3ኛ ሩብ ዓመት | | | ሪፖርቱ እስከሚሸፍነው ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% |
| | ከሰው ሰራሽ ደንና ከደን ተረፈ ምርቶች በተሻሻለ ዘዴ የተመረተ ከሰል መጠን | ሚሊ/ቶን | 0.345 | 0.2 | 0.067 | 0.067 | 100 | 0.134 | 0.219 | 100 |
| | ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የቀረበ የደን ምርት መጠን | ቶን (ሚሊዮን) | 2.34 | 1.02 | 0.34 | 0.9152 | 100 | 0.68 | 1.8552 | 100 |
| | በደን ዘርፍ ስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች ብዛት | በሚሊዮን ቁጥር | 0.255 | 0.25 | 0.1 | 0.064 | 64 | 0.22 | 0.26 | 100 |
| | ከደን ሮያሊቲ የተገኘ ሀብት መጠን | በሚሊዮን ብር | 293.1 | 250 | 70 | 101.957 | 100 | 180 | 246.699 | 100 |
| | ከደን ምርት ኤክስፖርት የተገኘ እና በሃገር ውስጥ የደን ምርት ምክንያት የዳነ የውጭ ምንዛሪ መጠን | በሚሊዮን ዶላር | | 20 | 6 | 9.608 | 100 | 13 | 17.29 | 100 |
| | ኑሮአቸውን በደን ላይ መሰረት ያደረጉ የህብረተሰብ ክፍሎች መጠን የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | - | 1 | 1 | | | 1 | | |
| | የደን ኢንተርፕራይዞችን እና ኢንዱስትሪዎችን ያለባቸውን ችግሮች ለመለየትና ለመደገፍ የተደረገ ክትትልና ድጋፍ | በቁጥር | - | 4 | 1 | 1 | 100 | 3 | 3 | 100 |
| | **ግብ 8. የደን መረጃና ቴክኖሎጂ ማመንጨትና ማላመድ** | | | | | | | | | |
| | **በምርምር የወጡ ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎች** | | | | | | | | | |
| | **መረጃዎች** | **በቁጥር** | **31** | **42** | **6** | **6** | 100 | 13 | 12 | 92.3 |
| | **በሂደት ላይ ያሉ የምርምር ስራዎች ብዛት** | **በቁጥር** | **70** | **104** | **104** | 103 | 99 | 104 | 103 | 99 |
| | **በሰው ሰራሽና ጥምር ግብርና ደን ምርምር** | የምርምር ውጤቶች ብዛት በቁጥር | | | **3** | **4** | | **7** | **6** | |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 ኢላማ | የ3ኛ ሩብ ዓመት | | | ሪፖርቱ እስከሚሸፍነው ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% |
| | የጥምር ደን ግብርና አሰራሮችን የሚያሻሽሉ የምርምር ስራዎች ብዛት | ቁጥር | 29 | 20 | 20 | 19 | 85 | 20 | 19 | 85 |
| | የነጭ ባህር ዛፍ የመትከያ ርቀት በእድገት መጠን እና በእንጨት ባህሪይ ላይ ያለዉ አስተዋጽኦ መረጃ | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| | የቀረሮ ዛፍ በቁርጥራጭ የሚባዛበት ዘዴ መረጃ | ቁጥር | | 1 | | | | 1 | 1 | 100 |
| | የጥቁር እንጨት እድገት ሙከራ ብዛት | ቁጥር | | 1 | | | | 1 | 1 | 100 |
| | የማህበረሰብ የችግኝ ፍላጎትን በአይነት እና በመጠን በመለየት የወጣ መረጃ | ቁጥር | | 3 | | 1 | | 3 | 2 | 67 |
| | የሰው ሰራሽ ደን የምርምር ስራዎች ብዛት | ቁጥር | 31 | 24 | 24 | 22 | 92 | 24 | 22 | 92 |
| | ውርጭ በሚበዛባቸው ከፍተኛ ቦታዎች ላይ አዲስ የተቋቋሙ የችግኝ አፀዳደቅ ሙከራዎች ብዛት | ቁጥር | 2 | 3 | | | | 3 | 3 | 100 |
| | በወንዝ ዳርቻ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚሳይ መረጃ | ቁጥር | | **1** | **1** | **1** | 100 | **1** | **1** | 100 |
| | በወንዝ ዳርቻ የሚገኙ የዛፍ እና የቁጥቋጦ ዝርያዎችን ስብጥር የሚያሳይ መረጃ | ቁጥር | | **1** | **1** | **1** | 100 | **1** | **1** | 100 |
| | በዛፍ የታገዘ የተፋሰስ አያያዝ እና የተጎዱ መሬቶች ማገገሚያ የምርምር ስራዎች ብዛት | ቁጥር | 7 | 9 | 9 | 8 | 89 | 9 | 8 | 89 |
| | **በደን አጠባበቅ ምርምር** | | | | | | | | | |
| | የዛፍ ዝርያዎችን የሚያጠቁ ነፍሳተ ተባይ ላይ የተካሄዱ የምርምር ስራዎች ብዛት | በቁጥር | | 4 | 4 | 4 | 100 | 4 | 4 | 100 |
| | በዛፍ በሽታዎች ላይ የተካሄዱ የምርምር ስራዎች ብዛት | በቁጥር | | 3 | 3 | 3 | 100 | 3 | 3 | 100 |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 ኢላማ | የ3ኛ ሩብ ዓመት | | | ሪፖርቱ እስከሚሸፍነው ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% |
| | የተፈጥሮ ደን ቦታዎች የእሳት ቀጠና፣ ባህርይ እና ጸባይ/ሁኔታ ለማወቅ የተካሄዱ የምርምር ስራዎች ብዛት | በቁጥር | | 1 | 1 | - | - | 1 | - | - |
| | **በዛፍ ዘር ቴክኖሎጅ ምርምር** | | | | | | | | | |
| | የዛፍ ዘር ምንጭ ሙከራዎች ብዛት | ቁጥር | | 5 | 5 | 5 | 100 | 5 | 5 | 100 |
| | **የተፈጥሮ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ምርምር** | የምርምር ውጤቶች ብዛት በቁጥር | | | 3 | 2 | | 6 | 6 | |
| | የተፈጥሮ ደን ውስጥ የሚገኙ የዕጽዋት አይነትና ስብጥር የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | 1 | 100 |
| | የ13 ዛፍ ዝርያዎች የአበባ እና የፍሬ ወቅት ጊዜ የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | | 1 | |
| | የ4 ዛፍ ዝርያዎች የዘር የአበቃቀል ባህሪ የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | 1 | 100 |
| | የተቀናጀ የተፋሰስ ስራዎች በዝዋይ እና ጣና ሀይቆች ስነ-ምዳር መስተጋብር ላይ የሚያስከትለውን አወንታዊ ተጽዕኖ ለመገምገም የሚያስችል የተካሄደ የምርምር ሙከራ ብዛት | ቁጥር | | 8 | 8 | 8 | 100 | 8 | 8 | 100 |
| | በተፈጥሮ ደኖች ምርምር በማካሄድ የተለያዩ መረጃዎችን እና ቴክኖሎጂዎችን ለማመንጨት የተካሄደ የምርምር ሙከራ ብዛት | ቁጥር | | 17 | 17 | 17 | 100 | 17 | 17 | 100 |
| | የወራሪ ዕጽዋት በተፈጥሮ ደኖች ላይ ያስከተለውን ተጽዕኖ የሚያሳይ መረጃ እና የወራሪ ዕጽዋቶች ለመቆጣጠር የሚያስችል ቴክኖሎጂ ለማመንጨት የተካሄደ የምርምር ሙከራ ብዛት | ቁጥር | | 3 | 3 | 3 | 100 | 3 | 3 | 100 |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 ኢላማ | የ3ኛ ሩብ ዓመት | | | ሪፖርቱ እስከሚሸፍነው ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% |
| | ከሰል በማመረት ሂደት ውስጥ የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዝና ንጥረ ነገርን የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | 1 | 100 |
| | ለማገዶ የሚሆኑ ጥናት የተደረገላቸው 4 የዛፍ ዝርያዎች መረጃ | በቁጥር | | 1 | 1 | | | 1 | | |
| | በተጎዳ መሬት ላይ ባዮቻርን በመጠቀም በችግኝ እድገት እና በአፈር ር ካርቦን መጠን ላይ ያለውን ፋይዳ ለማወቅ የተካሄደ የምርምር ሙከራ ብዛት | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| | በላይኛው አዋሽ ተፋሰስ ላይ የመሬት አጠቃቀም እና የደን ሽፋን ለዉጥን የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| | አየር ንብረት ለውጥ በመጥፋት ላይ ባሉ ሁለት የዛፍ ዝርያዎች እድገት ላይ ያለውን ጫና የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| | **በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ምርምር** | | | | | | | | | |
| | የዲማ(ባኦባብ)፣ ጊሽጣ፣ የበረሃ ሎሚ፣ እንኮይና ሮቃ ዝርያዎችን የማላመድ ሙከራዎች ብዛት | በቁጥር | | 3 | 3 | 3 | 100 | 3 | 3 | 100 |
| | የቦሶሊያ ፓፕሪፌራ እና ሴኒጋል ግራር የማድማት ሙከራዎች ብዛት | በቁጥር | | 2 | 2 | 2 | 100 | 2 | 2 | 100 |
| | የደጋ፣ የቆላ እና ከውጭ የገቡ የቀርከሃ ዝርያዎች የማላመድ ሙከራዎች ብዛት፣ | በቁጥር | | 4 | 4 | 4 | 100 | 4 | 4 | 100 |
| | የአኬሽያ ካፍራ ጣውላ አውዳሚ ተባዮችን የመቋቋም ምርምር ሙከራዎች ብዛት፣ | በቁጥር | | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| | **ግብ 9. የመረጃና ቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ** | | | | | | | | | |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 ኢላማ | የ3ኛ ሩብ ዓመት | | | ሪፖርቱ እስከሚሸፍነው ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% |
| | **የተዘጋጁ የምርምር ውጤቶች የትግበራ ፓኬጅ ብዛት** | **በቁጥር** | | 41 | | 17 | | | 36 | |
| | በሰው ሰራሽ እና ጥምር ግብርና ደን | በቁጥር | | 10 | | 12 | | | 13 | |
| | በስርዓተ-ምህዳር (ተፈጥሮ ደን) | በቁጥር | | 8 | | | | | 6 | |
| | በአየር ንብረት ሳይንስ | በቁጥር | | 5 | | | | | 8 | |
| | በሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ፣ ፖሊሲ ኤክስቴንሽን | በቁጥር | | 7 | | 5 | | | 7 | |
| | የዛፍ ዘር ቴክኖሎጂ | በቁጥር | | 2 | | | | | 2 | |
| | **በታወቁ ጆርናሎች ላይ የታተሙ የምርምር ውጤቶች** | **በቁጥር** | | 22 | 6 | 7 | 100 | 6 | 11 | 100 |
| | ተፈጥሮ ደን እና አየር ንብረት ለውጥ | በቁጥር | | 7 | 3 | 3 | 100 | 3 | 4 | 100 |
| | በሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ፣ ፖሊሲ | በቁጥር | | 3 | 1 | 2 | 100 | 1 | 2 | 100 |
| | የዛፍ ዘር ቴክኖሎጂ | በቁጥር | | 3 | 1 | 1 | 100 | 1 | 3 | 100 |
| | የደን ውጤቶች | በቁጥር | | 3 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| | የደን አጠባበቅ | በቁጥር | | 1 | | | | | 1 | |
| | **ተጠቃሚዎች በቴክኖሎጂ ቅድመ ማስፋፋት የተሰጠ ስልጠና** | **በተሳታፊ ቁጥር** | | 200 | 100 | | | 100 | | |
| | **ግብ 10. የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ** | | | | | | | | | |
| | የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ሴቶች ቁጥር | በቁጥር (ሚሊዮን) | 0.072 | 0.063 | 0.031 | 0.016 | 51.2 | 0.0535 | 0.0768 | 100 |
| | የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ወጣቶች ቁጥር | በቁጥር(ሚሊዮን) | 0.122 | 0.125 | 0.05 | 0.032 | 64.2 | 0.2 | 0.1818 | 91 |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 ኢላማ | የ3ኛ ሩብ ዓመት | | | ሪፖርቱ እስከሚሸፍነው ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% |
| | የተዘጋጀ የህፃናት ማቆያ | በቁጥር | | 2 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| | የሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች አካቶ የተሰጠ ሥልጠናዎች ብዛት | በቁጥር | | 2 | - | 1 | - | 1 | 1 | 100 |
| መማማርና ዕድገት | **ግብ 11. የዘርፉን የመሰረተ ልማት ሽፋን ማሳደግ፣** | | | | | | | | | |
| | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ማዕከል G+5 ላቦራቶሪ ግንባታ ስራ ያለበት ደረጃ | በመቶኛ | 15 | 100 | 70 | 25.84 | 36.9 | 70 | 25.84 | 36.9 |
| | የደን ዉጤቶች እኖቬሽን ማዕከል ላቦራቶሪ ኮምፕሌክስ G+3 ግንባታ ስራ ያለበት ደረጃ | በመቶኛ | 40 | 100 | 80 | 45.47 | 56.8 | 80 | 45.47 | 56.8 |
| | የተጠናከሩ የምርምር ሙከራ ጣቢያዎች ብዛት | በቁጥር | | 2 | | | | 2 | 2 | 100 |
| | እንክብካቤ የተደረገላቸው ነባር የዛፍ ዘር ምንጮች | በሄክታር | 371 | 371 | 371 | 371 | 100 | 371 | 371 | 100 |
| | የመስክ መሳሪዎች አቅርቦት ፣ እድገት | ቁጥር | | 120 | | | | 120 | | |
| | • ካሊፐር ትልቁ | ቁጥር | | 30 | | | | 30 | 70 | 100 |
| | • ካሊፐር ትንሹ | ቁጥር | | 10 | | | | 10 | 70 | 100 |
| | • ጂፒኤስ | ቁጥር | | 20 | | | | 20 | 70 | 100 |
| | • ክሊኖሜትር | ቁጥር | | 20 | | | | 20 | 70 | 100 |
| | • ሜትር | ቁጥር | | 20 | | | | 20 | 70 | 100 |
| | • ዲያሜትር ቴፕ | ቁጥር | | 20 | | | | 20 | 70 | 100 |
| | የሰረቨር ፓወር ባንክ (UPS) | ቁጥር | | 2 | | | | 2 | 2 | 100 |
| | አውቶሜት የተደረጉ የተቋሙን አሰራሮች | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | 1 | 100 |
| | የተሻሻለ የዛፍ ዘር ምንጮች ፖረታል እና የዛፍ ዘር ትስስር ኔትዎርክ | በቁጥር | | 2 | 2 | 2 | 100 | 2 | 2 | 100 |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 ኢላማ | የ3ኛ ሩብ ዓመት | | | ሪፖርቱ እስከሚሸፍነው ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% |
| | በመካሄድ ላይ የሚገኙ የምርምር ችግኝ ጣቢያዎች ብዛት | ቁጥር | 8 | 8 | 8 | 8 | 100 | 8 | 8 | 100 |
| | ግብ 12. የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ፣ | | | | | | | | | |
| | የአጭር ጊዜ ስልጠና ያገኙ ሰራተኞች | በቁጥር | | 265 | 100 | 239 | 100 | 265 | 717 | 100 |
| | የአጭር ግዜ ስልጠና ያገኙ ተመራማሪዎች | በቁጥር | | 164 | | | | 164 | 40 | 24.4 |
| | የረጅም ጊዜ ስልጠና ላይ የሚገኙ ሠራተኞች | | | | | | | | | |
| | የመጀመሪያ ዲግሪ | በቁጥር | | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| | በሁለተኛ ዲግሪ | በቁጥር | | 48 | 48 | 48 | 100 | 48 | 48 | 100 |
| | በሶስተኛ ዲግሪ | በቁጥር | | 25 | 25 | 25 | 100 | 25 | 25 | 100 |
| | ስልጠና ያገኙ አመራሮች ብዛት | ቁጥር | | 60 | | | 60 | | | |
| | የተካሄደ የልምድ ልውውጥ ብዛት | በቁጥር | 1 | 2 | 1 | 1 | 100 | 2 | 2 | 100 |
| | አማካይ | | | | | | | | | 95.8 |

ማሳሰቢያ፡- በአመታዊ ዕቅድ ውስጥ ያሉ ነገር ግን በዘጠኝ ወር ውስጥ በዕቅድ ያልተያዙ ስራዎች በዚህ ሰንጠረዥ ውስጥ አልተካተቱም፡፡